መልእክት ሁለት
በምድሪቱ ላለህ የሰው ዘር በሙሉ

ተጻፈ ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ. ም. እ. ኤ. አ.

ይህ ሁለተኛ የፈጣሪ ውሳኔ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

ወይም

ቀይ መብራት የታየበት ሊባል ይችላል።

<u>ማስታወሻ</u>

.. መልእክቱን በጥንቃቄ ያንብቡ

.. ለሌሎች ሲሰጡ ሁሉንም ገጾች ይስጡ። አይጨምሩ፣ አይቀንሱ፣
አያሻሽሉ፣ ይህን የሚያደርጉ አለቅጣት አይታለፉምና !

.. እኔ በነጻ እንደሰጠኁአችሁ እናንተም በነጻ ስጡ ፈቅዶ ወዶ ከሰጡአችሁ ተቀበሉ።
በረከቱ ይበልጥብናል ካላችሁ አትቀበሉ።

.. ፋከስ አድርጉት፣ ኢሜይል አድርጉት፣ በድረገጾቻችሁ ልቀቁት፣ በፖስታም ላኩ።

.. በጋዜጣ በመጽሔት አትሙት፣ አሰራጩት በሬድዮን፣ በቴሌቪዥን ልቀቁት

.. እንደ ትዕዛዙና ምክሩ ለማያደርጉ በትዕዛዙ ውሰጥ የሚገጥማቸውን ያንብቡ።

.. በጎ ለመስራት ማንም አይከለከልም።

.. መሪም ሆነ ተመሪ ሁሉም የሚመዘነው እንደመጸጸቱና እንደቅን ተግባሩ ነው።

.. በጎ ሥራም የሚጀመረው ከትንሹ ነው።

መልካም የመረዳት ንባብ ይሁንልዎ !

ግንቦት 27/2000 ዓ. ም ተጻፈ

በምድራችን ሁሉ ፊት ተበትኖ ለሚኖር

መላው የአዳም ዘር በሙሉ

ሁለተኛውና የመጨረሻው መልእክት ነው ሌላ የሚመጣ የለም፡፡ የተወሰነውን ወደ ተግባር ከሚለውጥ በስተቀር፡፡

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን !

ትእዛዝህን ፈልጌአለሁና

አስፍቼ እሄዳለሁ

በነገስታት ፊት ምስክርህን እናገራለሁ አላፍርምም

እጅግ በወደድኑአቸው በትእዛዛትህ ደስ ይለኛል

እጆቼንም ወደ ወደድኑአቸው ወደ ትእዛዛትህ አነሳለሁ

ስርአትህንም አሰላስላለሁ መዝ. 118 (119) 44 – 48

እንዳለው ዳዊት ለሁሉም የሰው ዘር ! የፈጣሪን የፍርድ ውሳኔና ሂደት እንድታደምጡ እነሆ ታዘዝሁ፡፡ ትእዛዜንም ያለአንዳች ፍረሃት እነሆ የሰው ዘር በሙሉ አድምጥ፣ ጆሮህን፣አይንህን ክፈት ብዬ እናገራለሁ፡፡ በአእምሮአችን የሚታወቀውንም፣ የማይታሰበውንም፣ የማይደረስበትን፣ የረቀቀውን፣ ተገለጸውንም፣ የገዘፈውን፣ ያነሰውንም፣ ሁሉንም የፈጠረ አምላካችን ስሙ ይባረክ ! ያለ የሚኖር የዘመንም የጊዜም የሁሉ ነገር ፈጠሪ አምላክ ለስሙ ክብር ይሁን፡፡ የብርሃን ፈጣሪና ጌታ እግዚአብሄር ማንም በማይቀርበው ብርሃን ውስጥ ዙፋኑን የዘረጋ አምላካችን የተመሰገነ ይሁን፡፡

ሰውን ለክብሩ፣ ሊመሰገንበት፣ በራሱ አምሳል አክብሮ የፈጠረ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ለዘላለም እስከዘላለም ሊመሰገን ይገባዋል፡፡ ልንከብር፣ ልንድን፣ የዘላለም ህይወት ልንወርስ፣ የወደደን ቸሩ ፈጠሪ ይመስገን፡፡ ማንም የማይመክረው ፣ ማነም የማያዘው፣ ፈቃዱ የወደደችውን ሁሉ የሚያደርግ አምላክ ይክበር ይመስገን፡፡ በባህርዩ እውነትን፣ ፍቅርን፣ ቸርነትን፣ ፈጹምነትን የለበሰ፣ ፍጹም የሆነ ጌታ ለክብሩ ስለ ፈጠረን ልናመሰግነው ይገባል፡፡ የዘላለም ህይወት ልንወርስ ከመንግስቱ ሙላት በደስታ ልንቦርቅ ፍጹም የወደደን ማንም በማያልፈው መከራ ስጋውን በጣጥሶ ደሙን ዘርቶ በታላቅ ሰቆቃ ሞትን ጨልጦ በ 3 ቀን የሞትን ጀግንነት በትኖ (ድል ነስቶ) እሰከ ምን ርቀት እንደሚወደን አሳይቶን በክብሩና በዙፋኑ ላይ ያለ ጌታ የተመሰገነ ይሁን !!

መዝሙረ ዳዊት 103 (104)

ከእናታችን ከድንግል ማርያም ስጋዋን ቆርሶ ደምዋን ወርሶ ፍጹም ሰው ሆኖ፣ የኛ ህመም ህመሙ፣ ቁስላችንን፣ መሰበር፣ መነሳቆል፣ መድቀቅን ሁሉ ገንዘቡ አድርጎ ልናልፍበት ልንከፍለው የሚገባንን የሃጢያት ዋጋ ሁሉ ራሱን ሰውቶ ፍጹም ዋጋ ከፍሎ ላዳነን፣ ለክብሩ ላበቃን፣ የገሃነም ደጆች ሊያጠፏት የልቻሏትን፣ የተዋህዶ አርቶዶክስን እምነት በዚህ ሁሉ የጥፋት ማእበል ውስጥ አጽንቶ ላቆመልን፣ አምላካችን ክብር ምስጋና ውዳሴ በፍጹም ነፍሳችን ከፍጹም ሃሳባችንና ከፍጹም ልባችን ለሱ ይፍሰስ ! ስሙ ይባረክ አሜን !!

የዛሬው መልእክቴ የመጨረሻና ማሳረጊያዬ ነው

ደግሜ እላለሁ የመጨረሻው መልእክት ነው

የመልእክቱ ጭብጥ በሁለት ይከፈላል፡፡ 1ኛው መልክት በመላው አለም ያሉ አገራትንና ህዝባቸውን የሚመለከት ሲሆን፡፡ 2ኛው የአገሬን የኢትዮጵያን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ ከትእቢትና ንቀት ርቃችሁ ልብ ብላችሁ አድምጡ ! የፍርድ ቃልና ውሳኔ ሊፈጸምባቸው የተዘጋጀና በየደጃችሁ መቆሙን እንድታውቁት የታዘዘ ቃል ነው፡፡

ከኢትዮጵያ ውጭ ላሉ የአለም ህዝብ በሙሉ እንዲዳረስ በእንግሊዝኛ ይሄው መልእክትና የፍርድ ቃል ቀርቧል፡፡

ሰው ሆይ አድምጥ

መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 1 ፡ ም 2 ፡ 1 – 10

መዝሙረ ዳዊት 18 (19)

መዝሙረ ዳዊት 32 (33) 16 – 22

ፈጣሪውን ለናቀ ትእዛዙንና ፈቀዱን ላቃለለና በፍጹም የዲያብሎስ ተገዥ ለሆነ ህዝብ የግድ ፍርዱን ሊያገኝ የገባል፤ ቢወቀስ ቢገሰጽ ቢገረፍ በፍጹም የማይሰማ ፤ ከአንዱ ጥፋት ወደ ሌላው የሚሸጋገር የፈጠረውን አምላክ ትእግስት የሚፈታተን፣ አልፎም የሚሳደብ፣ በያዘው እውቀት የሚታበይና እራሱን ከፈጠረው ጌታ በላይ ያደረገ፣ የዘመኑ ሰው የግድ የፈለገውን እሬቱን ሊጋተው ይገባል፡፡

መዝሙረ ዳዊት 10

ከሌሎች ፍጥረቶች ሁሉ ትለያለህና በፈጣሪ አምሳል የተፈጠርክ ሰው ነህና እንደ ስብእናህ አስብና አድምጥ፤ ጆሮህን ክፈት፣ አይንህም ይገለጥ፤ በገደል ጫፍ ላይ ቆመሃል፣ ልትተፋ ልትጣል ነው፡፡ የዘላለምን ጨለማ የዚችንም አለም እንግድነት በውርደት ልትጨልጥ ነው፡፡ አስተውል፣ አስብ፣ ፈጥነህ አድምጥ ይህ መልዕክት የኖቤል ፕራይዝ እያልክ የምትሸላለምበት ድርሰት፣ ልብወለድ እንዳይመስልህ፡፡ ይህ መልእክት የፍርድ ነው፡፡ ሰማይና ምድርን የፈጠረና የዘረጋ አንተንም ፈቅዶ የፈጠረ አምላክ ውሳኔ ነው፡፡ ከአፉ ወጣ ቃሉ፤ የታዘዘውን ሰይፈጽም አይመለስም፡፡ ቃሉ ከሚታጎል ምድርና ሰማይ ቢያልፉ ይቀላልና !

በምድርም ከንቱ በመጭውም ዓለም ውዳቂ ለምትሆን ላንተ መጥቶብሃልና፤ ምጥ ጀምረሃል፡፡ ረሃብ፣ ጦርነት፣ አውሎ ንፋስ፣ ማእበል፣ እሳተ ገሞራ ሁሉም የፈጠራቸውን የአምላካቸውን ትእዛዝ ለመፈጸም ተጠንቀቅ ቆመዋል፡፡

መንግስት ነኝ፣ ድርጅት ነኝ፣ መሪ ነኝ፣ ካቶሊክ ነኝ፣ እስላም ነኝ፣ ፕሮቴስታነት ነኝ፣ አለም አቀፍ ድርጅት ነኝ፣ ፕሮፌሰር ነኝ፣ ዶክተር ነኝ፣ ጀነራል ነኝ፣ ሊቅ ነኝ፣ ባለ ታንክ፣ ባለ ጀት፣ ባለ ኒውክሊየር፣ ብዙ ሃብት አለኝ፤ ለምትል በንቀት፣ በትእቢት፣ በአውቀለሁ ባይነት ለተሞላህ፤ ውሸትን እንደጥበብ ለለበስክ ጨካኝ ነፍስ ገዳይ ለሆንክ ሁሉ ትቢያ ነህ አትጠራጠር፤ ወደ ትቢያ ትመለሳለህ፣ መና ነህ፣ እንደ ጢስ ትበናለህ፤ የፈጣሪን ቁጣ የቀሰቀሰው አመፅህ የሚበላህን እሳት ወልዱአል፡፡ ይበላሃል አታመልጥም፡፡

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ይህን አስቡአል የሚያስጥለውስ ማነው? እጁ ተዘርግታለች የሚመልሳትስ ማነው? ኢሳኢያስ 14፡ 27

ማንኛውም ይህ መልእክት የደረሰው ሰው ለሌላው ወገኑ ሳያነል ሳይጨምር ሊያደርስ ይገባዋል፡፡ ለሁሉም እንዲደርሰው አቅምህ የፈቀደውን ሁሉ አድርግ፤ ለፈጣሪ መታዘዝ ማለት፣ ሌላው ወንድምህና እህትህ የሚድኑበትን፣ ከሞት አደጋ የሚያመልጡበትን ሁሉ ማድረግ ነው፡፡ በቅንነት በየዋህነት የፈጠሪውን ትእዛዝ በማከበር ለሚለፋ ዋጋው ይከፈለዋል፡፡ ይህ መልእክት ለሁሉም የሰው ዘር ሊደርሰው ይገባዋል፤ ቢቀበልም ባይቀበልም፣ ቢሰማም ባይሰማም፣ አንተ ፈጣሪ የጣለብህን አደራ ተወጣ፡፡ ንገረው አልሰማ ካለ እጅህን አጨብጭበህ የእግርህን ትቢያ አራግፈህ ፤ አንተ እንዳራገፍከው ሁሉ የሰረዊት ጌታ እግዚአብሄርም እንደዚሁ እንደ ትቢያም ይበትነዋል፡፡ ስለዚህ አንተ መልእክቱን አድርስ፤ ቢፈልግ ይጣለው፣ ይቅደደው፣ ይተችም፣ ይመጻደቅም፣ እንደለመደም፣ የክርክር፣ የፍልስፍና አጀንዳም ይከፈትበት፣ ያሻውንም ይበል፣ የሚከፈለው ዋጋ በእግዚአብሄር እጅ ነው፡፡ በመሆኑም ሳይውል ሳያድር ዋጋውን ይቀበላል፡፡ አላግጦ ንቆ አሹፎ የሚኖርበት ዘመን አልቆአልና ! ማንኛውም ሰው ይህን መልእክት ካነበበ በኋላ ቀድሞ እራሱን ቢያይ መልካም ነው፡፡ ብዙዎች እንደ ህይወታቸው ልምድና እንደ እውቀታቸው፣ እንደ ተግባራቸው ሊያዩና ሊተረጉሙ ይችላሉ፡፡ ይህ በዚህ ገሃድ አለም በሚፈጠር የስጋ ጭቅጭቅ የሚፈቀድና የተለመደ ነው፡፡

ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ድካማችሁ በጌታ እግዚአብሄር ከንቱ እንዳይሆን አውቃችሁ የምትደላደሉ ፣ የማትነቃነቁም፣ የጌታ ስራ ሁል ጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ!! ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች - ፩ ም 15 -58

ይህ የምታነበው ቃል ከፈጣሪ ጋር የቀረበ ግንኙነት ባላቸው በተልእኮው በታመኑ አገልጋዮቹና ባሮቹ የተጻፈ የሚወቅስህ፣ ባትሰማ ባትመለስ ዋጋህን የሚሰጥህ የፍርድ ቃል ነው፡፡ በስጋ ምኞት፣ በግል ስሜት የመጣ እንዳይመስልህ እዚህ ውስጥ የምትሰማውና የምትረዳው መልዕክት አንዱም ነጥብ ሳይወድቅና ሳይለወጥ ይፈጸማል፡፡ ቆሞ ተርፎ ለማየት ያድልህ እንጂ፡፡ በእርግጥ መታወቅ የሚገባው እውነቱን አውቀህ ላልተመለስክ ልክ እንደ ኖህ ዘመን ሰዎች ጥፋቱ አንገተህ ደርሶ ተፀጽተህ ወደማትመለስበት ጫፍ ሲያደርስህ በዚያ ሰአት ብቻ ታውቀዋለህ፡፡ ይህ ቃል እውነት መሆኑን ወደ ሞት እየተላለፍክ ለነፍስህ፣ ለራስህ፣ ለውስጥህ ነግረህ ትከትማለህ ሰለዚህ ስማ !

ትንቢተ ኢሳኢያስ ምዕ ፡ 2፡ 6 – 22

ትንቢተ ኢሳኢያስ ምዕ ፡ 5፡ 7 – 30

የአዳም ዘር አድምጥ ፍርድህ ወጥቶአል፡፡ ማምለጫ የለም፡፡ በ1988 ዓ.ም. በህዳር 7 ቀን በኢትዮጵያ አቆጣጠር በ 21 ገጽ የተከተተ የመጀመሪያው መልእክት የላከሁ ሲሆን ታላላቅ አገርና የዚያም መሪ ነን ለሚሉ የስጋው መሪዎች፣ መንፈሳዊ መሪ ነን ለሚሉ በአደራ ፖስታ እንዲደርሳቸው ልኬላቸዋለሁ፡፡ በአዲስ አበባ ለሚገኙ የ17 አገሮችና አለም አቀፍ ድርጅቶች እዚህ ባኖሩአቸው ኤምባሲዎቻቸው በኩል በአደራ ፖስታ በአድራሻቸው ልኬአለሁ፡፡ በአገሬ ለብዙዎች በግል እንዲደርሳቸው አደርጌአለሁ፡፡ ለመላው ህዝብም በየቋንቋው ተርጉማችሁ እንድትገልጹ አሳስቤአለሁ፡፡ ሃላፊነትም እንደምትወስዱ ገልጫለሁ፡፡ ይህንን ንቃችሁ ይህንን ሳታደርጉ ቀርታችኋል፡፡ የሚገርመው አንድም የመንግስት ድርጅት፣ መንፈሳዊ ተቋም፣ ተብዩ ለወገኖቹና ለሚመረው ህዝብ የገለጸው የለም፡፡

ይሁንና ዛሬ በአለማችን ከ2 አመት ወዲህ እየተከሰተ ያለውን የምጥ ጅማሮ ሰትመለከቱ ቆይታችኋል፡፡ ይህም አይቆጠቆጣችሁም፡፡ ስለዚህ የዛሬው የሞት መርዶ መጥቶልሃል !!

የአባታችሁ የዲያብሎስ ሰራ፣ የዘፈን፣የዳንስ፣ የፊልም፣ የስፖርት፣ የፍጅት፣ የአደጋ ዜና፣ ብታገኙ በሰከንድ በረጫችሁት ነበር፡፡ ይሁንና ለኔ አይገደኝም፤ ሊያውቅ የሚገባው በተለያየ መንገድ ደርሶት አውቆታል፡፡ ያላወቀውም አሁን እያወቀው ነው፡፡

በዚህ የመጀመሪያ መልእክት የሚገጥማችሁ በግልጽ ተነግሯል፡፡ ስራችሁም ተገልጧል የእሳት ባህር ይጠርጋችኋል፡፡ ይህም የአለምን የሙቀት መጨመር እየተመለከትከው ነው፡፡ በሳይንስ ትመልሰዋለህ ጠብቀው፡፡ ለሚያስተውል ራሱንና ወገኑን የት እንዳሉ የሚያይበት መነጽር ነው፡፡ አሁን ያ ወቅት ሳትጠቀምበት አልፏል፡፡ 2ኛ አመቱን አጠናቋል፡፡ መጪው ምንድነው የሚለውን መመልከት ተገቢም አስፈላጊም ነው፡፡ በመጀመሪያውም ሆነ በዚህ በ2ኛው መልእክት የተገለጸው ሁሉ ይፈጸማል፡፡ አንዳችም የሚቀር ነገር የለም፡፡ አለም የተለያየ መጠን ባላቸው ችግር ውስጥ ወድቃለች፤ ሙቀት ጨምሯል፣ረሃብ ነግሷል፣ ግጭት በዝቷል፣ የአየር ንብረት ተለውጧል፣ ምድር ባህሪዋን ለውጣለች፡፡ ይህ ሁሉ ልክ ነው፡፡ ይሄው ጥፋት በብዙ መቶ እጥፍ በከፍተኛ መጠን ይጨምራል፡፡ የዲያብሎስ ልጆች በእሳት ባህር ለመጠረጋቸው መጠራጠር የለባችሁም፡፡ የቻይናን ምድር ያንቀጠቀጠና ያፈረሰ፣ በርማን የጠረገ፣ የቁጣ ምልክት ምን ይመስላችኋል? እናንተ ጋ አይመጣም? የሚያግደው አለ? በሺ እጥፍ ይመጣልሃል፡፡ እንናተ ሞት ሲውጣችሁ ብቻ ነው የሚገባችሁ፡፡ ስለዚህ ጠብቁት፡፡

አንዲት እርጉዝ ሴት ልትወልድ ወሯ ሲገባ ይጎረብጣታል፣ ይወጋጋታል፣ጭንቅ ጭንቅ ይላታል፡፡ ይህም የምጥ መምጫው ምልክት ነው፡፡ ዛሬም በአለማችን የሚታየው ይሄው የጥፋት መምጣት ምልክቶች ናቸው፡፡ ታላቁ ምጥ ገና ይጀምራል፡፡ የትስ ታመልጣላችሁ ! ከጌታ ወዴት ትሸሸጋላችሁ ! እውቀታችሁ፣ ሃብታችሁ፣ ግንባችሁ መኪናችሁ አውሮፕላናችሁ፣ የቆፈራችሁት መደበቂየችሁ፣ ወታደራችሁ፣ ጥበባችሁ ለመሆኑ የቱ ነው ከፈጣሪ የቁጣ በትር ሸሽጎ የሚያኖራችሁ ! ረሃብና የኢኮኖሚው ችግር ለደሃ ብቻ እንደመጣ ትናገራላችሁ፤ ባለጠጎች ናችሁና በወርቃችሁ በብራችሁ እንድናለን ባዮች ናችሁ፡፡ ጠብቁ ! ውጤቱን ታያላችሁ፡፡ ከተደበቅህበት ፈትሾ ገብቶ የሚበላ እሳት ይመጣልሃል፡፡ ኢሳኢያስ ም . 13

በእግዚአብሄር ቤት መሸሸግ የሚቻለው ለምኖ ከፈጣሪ ለማስታረቅም ለመታረቅም ለሁሉም የሚበቃ መንፈሳዊነትና መንፈሳዊ አባቶች ሲኖሩ ነው፡፡ ከአለማዊው አመጽ ይበልጥ አመጽ የሚፈጸመው በእምነት መሪዎች ነው፡፡ ሶዶሚያውያን ናቸው፣ አመጸኞችና በጥበባቸው የሚመኩ፣ ለጨለማ ስራ ድጋፍ የሚሰጡ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ በጥቅሉ ለዲያብሎስ ስራ የተጉ ናቸው፡፡

ከተጣመመና የእግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስን ትምህርትና ፈቃድ፣ ከናቀና ካደፈረሰ፣ ከደለዘና ከለወጠ የድፍረት ትምህርታቸው በላይ አመጻቸው የበረታ ነው፡፡ ነፍሰ ገዳዮችን የሚባርኩ፣ በእምነት ሽፋን የፖለቲካን ስራ የሚሰሩ፣ ወደ ተለያየም

ስፍራ ሲሄዱ በቀሚሳቸው የረቀቀ የዲያብሎስን ተልእኮ ለማስፈጸም የሚተጉ ናቸው፡፡ እናንተና የእግዚአብሄር ትእዛዝ ወዴት ስትተዋወቁ ! ህንጻ ቢያምር እውነትን አያሳይ በረቀቀ ጥበብ ቢሰብክ አያንጽ፡፡ ውስጣቸሁ በአመጽ የተገነባና ለቢያብሎስ ፈቃድና ለጨለማ አሰራር የተገዛ በመሆኑ እንዴት መልካም ይወጣችኋል?

ትን ኢሳኢያስ 28 ፡ 3 – 29

የካቶሊኩ መሪና የእስልምና መሪዎች እርስ በእርስ በመጽሐፋቸው ሲመራረቁ የታየ ሲሆን የደም አፍሳሾችን መጽሐፍ እንደ መልካም ከቆጠረና ከዘከረ በምን መልኩ ነው መንፈሳዊ መሪ ሚሆነው? በሚመራቸው የእምነት ተቋሞች ሰዶማውያን ሞልተውበትና፤ የፖለቲካ ሰራተኛ በሆኑበት የእግዚአብሄር ፈቀድና ትእዛዝ በፈረሰበት እንዴት ነው ያላመነ የሚያምንበት? በምንስ መልኩ ነው የመንፈስ ስብራቱ የሚጠገንበት? በመጀመሪያው መልእክት እንደተገለጸው ብዙ የእምነት መጽሐፍትና የመስኩ ጠበብቶች አሏችሁ ብዙ ጽፋችኋል፡፡ እንደ ስጋው እውቀት እሰከ ዶክተር ማእረግ የሚያደርስ የቲዎሎጂ ትምህርት ማስረጃ ትሰጣላችሁ፡፡ ብጹእ፣ በጹእነታቸው ትባላላችሁ፤ጳጳስ የተከበሩ ትባላላችሁ፡፡ የከበሬታ ወንበር በሄዳችሁበት ሁሉ ለናንተ ነው፡፡ ልብሳችሁ ያማረ ነው፡፡ ዝማሪአችሁ በብዙ መሳሪያና የሰው ጩኸት የተመላ ነው፡፡ ፕሮቴስታንቱ፣ አንጀሊካኑም፣ እስላሙም፣ ቡዲስቱም፣ ሌላውም ሁሉ እንደናንተው ነው፡፡ ኤሌክትሮኒክ ሚዲያው የናንተ ነው፡፡ መሰብሰቢያው ሁሉ የናንተ ነው፡፡ እጅግ የበዛ ሃብትም ባለቤት ናችሁ፡፡ የዘመኑ ሊቀውንት የፖለቲካ መሪዎች ለጥፋታቸው ሲሰማሩ መርቃችሁ አበረታታችሁ የምትልኩ እናንተ ናችሁ፡፡

የእውቀታቸውም የጥበባቸውም አምላኪ ናችሁ፡፡ ልባችሁ ከነዚህ ከዲያብሎስ ልጆች ጋር ነው፡፡ ጀርባችሁን ለእግዚአብሄር ሰጥታችኋል፡፡ ለጸሎት በሚል ትሰባሰባላችሁ፡፡ ሰሚ የላችሁም፡፡ ፈጣሪ እናንተን ከሚያዳምጥ ጆሮውን ከደፈነ ቆየ፡፡ እንደ ፋንድያ ጭስ የሚሸተውን ጩኸታችሁን እንኩአን ሊየዳምጥ ሊታገሳችሁና ሊሸከማችሁ ታክቶታል፡፡

የዳዊት መዝሙር 35 (36) ፡ 1 – 4

በአለማችን ላይ መልከ ብዙ እምነቶች ምድርን ሸፍነዋል፡፡ የጥፋት መንገድ ሰፊ፤ የመዳን መንገድ ጠባብ፤ መሆኑን ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ ሰፊው መንገድ የዲብሎስ መንገድ ነው፡፡ ስሙን ብቻ በለበሱ በውስጣቸው እውነት በሌለቸው የዲያብሎስ ልጆች የተሞላ ነው፡፡ ስማቸው ብዙ ነው፡፡ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት፣ እስላም፣ ቡዲዝም፣ ሺንቶኢዝም፣ ታኦኢዝም፣ ቁጥራቸው የበዛ ነው፡፡ አንዳንዶቹ የክርስትና ካባ የለበሱ ውስጠ ባዶ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ፍጹም ጣኦት የሚያመልኩ ናቸው፡፡ ሌሎቹም ፍልስፍና መሰል እምነቶች ናቸው፡፡ ከአለም 6 ቢሊዮን ህዝብ ቁጥር 90 በመቶ የሚሸፍኑ ናቸው፡፡ በድምጽ ብልጫ የፈጣሪን እጅ ሊጠመዝዙ እነደሚችሉ የሚያምኑና የሚገምቱ የሰይጣን ልጆች ናቸው፡፡

ይህ የሚያስታውሰው ባንዱ የእግዚአብሄር ሰው የሆነው ኤልያስና የእስራኤልን ህዝብ ይመሩ ከነበሩ ኤልዛቤልና አከአብ ከነ 400 የበአል ቀሳውስት ጋር የተደረገን ፍልሚያ ነው፡፡ በዚህ ፍልሚያ በብዙ ሺ የሚቆጠሩት የኤልዛቢል ልጆች የአከአብ ህዝቦች የቡኤል ዘቡኤል ካህናት በአንዱ ኤልያስ ላይ ዘምተው፤ በዚሁ በአንዱ የእግዚአብሄር የታመነ ባሪያ ተመትተዋል፡፡

በዘህ ንጽጽር ስናይ በአለም ሁሉ ፊት ከ5 ቢሊዮን በላይ የሚሆነው ህዝብ የተለያየ ስም አንጠልጥሎ ሁሉም በቀደመው ዲያብሎስ (እባብ) እየተመራ 99 በመቶ የአለም ህዝብ ከፈጣሪውእርቆ ከዚህ የዲያብሎስ አዝማቾች ጋር ቆሞአል፡፡ በተጻራሪው በቁጥርም በሃብትም በሁለመናዋ እጅግ ያነሰችው ሁሌም በነዚሁ የተቀጠቀጠችው የተዋህዶ አርቶዶክስ ቆማለች፡፡ ኤሊያስ ብቻውን ከፈጣሪው ጋር ቆመ፡፡ የኢትዮጵያ አርቶዶክስን በአለም ካሉ ጥቂት ወንድሞችዋ ጋር ከፈጠሪዋ ጋር፣ ከፈቃዱና ከትእዛዙ ጋር ቆማለች፡፡ ማን ያሸንፋል ኋላ እናያዋለን፡፡ የተውህዶ አርቶዶክስን እምነት በአሁኑ ሰአት በታላቅ ፈተና የወደቀች ከውሰጥም ከውጭም በጠላት የተወረረች በታለቅ ፈተና ላይ ያለች ነገር ግን የማትጠፋ የገሃነም ልጆች ሁሉ የከበቡአት ሆናለች፡፡

የመላው አለም የዲያብሎስ ፊት አውራሪና ሰረዊቱ በዚች የተዋህዶ እምነት ላይና የጸና መሰረቷን ባጸናችባት በአገሬ በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት የቆየና የሸበተ ሁለ ገብ ጦርነት አካሂደውባታል፡፡ እያካሄዱም ይገኛሉ፡፡ ዛሬም በአመራርዋና በውስጥዋ የተቀመጡት ከጠላት የወገኑ የጠላትን ፈቃድ በማስፈጸም ላይ የሚገኙ ሲሆን ከማእከል እሰከ መንደር ድረስ በዘለቀ እጅና እግራቸው የቤተክርስቲያንዋን መሰረትና ጽናት ለመናድ እየተጉ ይገኛሉ፡፡ የፖለቲካው መሳሪያ በመሆናቸው ከመንግስት ኃይሎች ጋር በመተባበር እያፈረሱ ለመሆናቸው ሁሉ የሚያውቀው እውነት ነው፡፡ ህዝቡም ፍጹም ስቶ የዘመናችንን የጥፋት ሰዎች ባህልና እምነት ወርሶ የዲየብሎስ ሰራተኛ ሆኖአል፡፡ አመንዛሪ ነው፣ ሌባ ቀጣፊ፣ ነፍሰ ገደይ፣ ሃሰት ተናጋሪና መስካሪ ነው፡፡

አምላካችሁ የሆነው የቀደመው እባብ ዲያብሎስ ለጥፋት አላማው ከእያት ቅድመ አያቶቻችሁ ጀምሮ እሰከ አሁን እየዘለቀ ባለው ጊዜ የተለያዩ የጥፋትና የጨለማ ሃጎቹን አስጨብጦአቸዋል፡፡ ሰማይና ምድርን የፈጠረውን አምላክ ፈቃድና ህግ ንቃችሁ በዲያብሎስ ህግና ፈቃድ የምትመሩ ሆናችኋል፡፡

ማመንዘር መብት ነው፣ መዋሸት ጥበብ ነው፣ የደሃን ፍርድ ማጣመም ትክክል ነው፣ ለባለሃብቱና ለባለስልጣኖች ቆሞ ድሃን ማሳደድና መበደል ፤ አግባብ ነው ብላችኋል፡፡ ዘረኝነትን፣ ሰዎችን በዘራቸው የበለይና የበታች ማድረግ፣ ሰዶማዊነት፣ የወሲብ እንዱስትሪ፣ የድሃን ጉልበትና ልፋቱን መንጠቅ የጥፋት መሳሪያ አዘጋጅቶ ህዝብን ማፋጀት፤ እኒህ በሙሉ ትክክለኛ ስራ ናቸው ብላችኋል !!

ባቢሎን (አሜሪካ)፣ ግልገል ባቢሎናውያን (አውሮፓ)የሚያወጡት ህግ የአባታቸው የዲያብሎስን በመሆኑ በዚህ በመመራት በጅምላም ሆነ በነጠላ የማይፈጽሙት ፍጅት የለም፡፡

ትንቢተ ኤርሚያስ ም 23 ፡ 9 – 40

ዛሬ ገንዘብ አምላክ ነው፡፡ በገንዘብ የማይገዛ ነገር የለም፡፡ የሁሉም ሰው ጣኦት ገንዘብ ነው፡፡ ዓለም በሙሉ ህልውናውን ለገንዘብ ሸጧል፡፡ ገንዘብ ደግሞ ዋነኛው የዲያብሎስ መሳሪያ ነው፡፡

ለዲየብሎስና ለናንተ ለጭፍሮቹ ብቻ የሚጠቅም የዲሞክራሲ መብት ትላላችሁ፡፡ አዘጋጅታችሁ ሁሉንም ህዝብ በዚህ ትነዳላችሁ፤ ለዚህ ዲሞክራሲ ለሚባለው ብሂልና ህጋችሁ አልገዛም ፤ በፈጠረኝ አምላክ ህግ ነው የምገዛው ያለውን ሰውም ሆነ ተቁአም ታሳድዳላችሁ፤ ትገላላችሁ፣ ታስራለችሁ ይህም ዘወትር የምትፈጽሙት ተግባራችሁ ነው፡፡

በአለም ላይ እንድንኖር የፈጠረን አምላክ የሰጠንን የፈቃዱን ህግና ስርአት በተዋህዶ አርቶዶክስ እምነት ጸንተው አባቶቻችን አልፈውበታል፡፡ ለእግዚአብሄር እውነት ተሰውተውበታል፡፡ የሚፈለገውንም ዋጋ ከፍለው አልፈዋል፡፡

ይኸው ተዋህዶ አርቶዶክስ እምነት በአገሬ ቆማ አልጠፋ ብላችሁ ፤ እነሆ እሷንም እንደ ድርጅት ለማጥፋት የተሳካላችሁ ሆኗል፡፡ እንደግል እምነት ግን በየሰው ልብ ውስጥ እግዚአብሄር ስለተከላት አልጠፋ ብላለች፡፡ ቫቲካን፣ ፕሮቴስታንት፣ ሙስሊም፣ ቡዲዝም፣ ሂንዱዚም፣ ኮንፊሽየስ ፣ ማናቸውም የእምነት ድርጅቶች ቅርጽ የያዘ በሙሉ ህልሙም፣ ጥረቱም፣ ዘመቻውም ይህቺን የእግዚአብሄር ቤት የእውነት ደጅ ፈጽሞ ማጥፋት ነው፡፡ ሁሉም የአለም ገዥዎች ፤ የእምነት መሪዎች በመሪያቸው በጨለማው ገዢ እየተመሩ ተዋህዶን ለማጥፋት ይደከማሉ፡፡ የሾሙአቸው፣ ያሳደጉአቸው፣ የኮተኮቱአቸው ጳጳሳት ስራቸው ይኸው ነው፡፡

ለዚህም ዛሬ በኢትዮጵያ ምድር ቁጥር የበዛ እስላም፣ ፕሮቴስታንት፣ ካቶሊክ ሌላም ሌላም የሞላው፡፡ ይህ ሁሉ የእምነት ተቁአምና ድርጅት ከጠዋት እስከ ማታ ዘምቶና አጥፍቶ የሚገባው የተዋህዶ አርቶዶክስ እምነትን ነው፡፡

ዘመቻቸው እመጨረሻው ጣሪያ ላይ በመድረሱ በውጭዎች የተተከሉት ጳጳሳት፣ ዲያቆናት፣ አገልጋይ ተብየዎች በተለያየ የዲያብሎስ የዘመቻ ስልት ተመርቀውና ተክነው ለሆዳቸው ያደሩ ሆነው የተለያየ የጠላት ዶክትሪን አንጠልጥለው እንደ ቅባት፣ ጸጋ፣ ተሀድሶ፤ የሚል የዲያብሎስ የረቀቀ ማጥፊያ አዝለው የማፍረስ ስራ መስራት ከጀመሩ ረጅም ዘመን ተቆጠረ፡፡ ከዚህ የዘለሉትን በሆዳቸው እንዲያስቡ ተደረገ፡፡ ለፖለቲካው መሳሪያ ሆኑ፣ ለፈጣሪ መገዛት ተዉ፡፡ ምዕመኑን ለአውሬ በተኑ፡፡ ሆዳቸውን ለመሙላት ከቅርስ ጀምሮ ማናቸውም ነገር ገንዘብ ያወጣል ብለው ያመኑበትን ሁሉ ሸጡ ለወጡ፡፡ አልጠፋም ያላቸው ከሰው ልብ ብቻ ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚቀናበረው ታዲያ ዓለምን እየነዳ ባለው የቀደመው እባብ ነው፡፡ ዙፋኑን በአሜሪካ፣በአውሮፓ፣ በኤሽያ፣ በመካከለኛው ምስራቅ ተከሎ ለተቀረው የአለም ክፍል እንደየአቅማቸው የሚመጥን ማዘዣ ጣቢያ አደራጅቶ ዓለምን ወደ ጥፋት እየነዳ ይገኛል፡፡ መቀመጫውና ማዘዣው በአለም የታወቁ ከተሞች ናቸው፡፡ ሁሉም ሰው እንደገነት የሚያያቸው ናቸው፡፡ እነኒዎርክ እነዋሽንግተን፣ እነለንደን፣ እነፓሪስ፣ እነብራስልስ፣ እነማድሪድ እነሊዝበን፣እነፔኪንግ፣ እነሞስኮ፣ እነቶኪዮ ወዘተ አይደሉም እንዴ ! በነዚህስ ከተሞች አይደለም እንዴ እንደሰናኦር ግንብ የረዘሙትን ህንጻዎችስ የምናየው ! በነዚህ ከተሞች ገዝፈው ከሚታዩት የአማሩ ህንጻዎች ፤ የነቫቲካን፣ የነፕሮቴስታንት የነአንጀሊካን፣ የነሙስሊም፣ የነቡድሃ አይደሉም እንዴ? የእምነት ዩኒቨርሲቲዎች ከሚሊዮን መጽሐፍቶቻቸው ጋር ያሉት የት ነው? ከነዚህ ከተሞች ውስጥ አይደለም እንዴ? መቼ ራሳቸውን ደበቁ በግልጽ የዲየብሎስን ስራ የሚሰሩ አኮ ናቸው፡፡ አለምንስ እንመራለን፣ እንዳኖለን ፣ እንወቅሳለን፣ እንቀጠቅጣለን፣ እናፈርሳለን እንገነባለን የሚሉትስ መሪዎች፣ጦረኞች ከነኑይከለራቸው፣ ከነጀታቸው፣ ከነሚሳኢላቸው እዚሁ አይደሉም እንዴ? በነዚህስ ከተሞች አይደለም እንዴ የምንዝርናው፣ የፊልሙ፣ የዘፈኑ፣ አስረህ ምቺው ኢንዱስትሪ የሞላው? አባታቸው ዲየብሎስ ቢሳካለት ገና ሰማይ ላይ ዙፋኑን ሊዘረጋ አይደለም የሚለፋው? ቋሚው ሳተላይት እስቴሽን ተብየው ለዚሁ ህልም አየደለም እንዴ የሚደክሙበት፡፡

ዓለምን የምታምሱበት የጥፋት መሳሪያዎቻችሁ ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ የሰው ልጅ ያስገነባው አይደለም እንዴ? ንዩክለር፣ ኒዩተሮን፣ ኬሚካል፣ ባዮሎጂካል፣ ሚሳኤሎች እጅግ የረቀቁ ጀቶች፣ ፈንጂዎች፣ ታንኮች ፣ መድፎች፣ በህዋ ላይ ደግሞ ኒዩክለር የታጠቁ ሳተለይቶች፣ በጨረር የሚጠቀሙ ማጥቂያ ሳተላይቶች ዓለምን ደጋግሞ ሊያጠፉ የሚችል መሳሪያ አከማችታችኋል፡፡ እየተጠቀማችሁበትም ነው፡፡

እናንተ የአመጽ ልጆች የፈጣሪን ትእግስት ንቃችሁ እንደሌለ እንድትቆጥሩት ሆናችሁ፡፡ ፈጣሪ የለምም ብላችሁ እንድታምኑና እንድታሳምኑ አድርጎአችኋል፡፡ ፈጣሪን እስከነመኖሩ ረስታችኋል፡፡ በአለም ሁሉ ምንዝርናን ስራ ያልሆነበትና እንደኢንዱስትሪ ያልተደራጀበት አገር አለወይ? እንኳን ምድር ባህሩም ነጻ ሊሆን አልቻለም፡፡ የምትመሩት በምድርና በባህር ውስጥ ባለው አጋንንት ብቻ አይደለም፤ በአየርም ከሚከንፈው የጨለማው ገዢ ጋር ጭምር ነው፡፡

ስለሆነም ይህ ሁሉ ተግባራችሁ ተመዘነ ቀለላችሁ፡፡ ዛሬም ትላንትም ከአያት ቅድመ አያቶቻችሁ ጀምሮ ለ 7000 (ሰባት ሺ) አመታት ስትመዘኑ ሰትለኩ አለፈ፡፡ በየመዝገባችሁ የሞላው የአመጽ ስራችሁ በሁሉም መስፈርት የሞት ፍርድን ወለደላችሁ፡፡ ለምህረትም የሚያበቃ ነገር ከውስጣችሁ ተፈልጎ ጠፋ ! እነሆም ፍርዱ ወጣ ተወሰነም፡፡

ዓለም አድምጥ !! ከእንግዲህ የናቅሃት ከነጭርሱም የማታውቃት ኢትዮጵያ በሰራዊት ጌታ ፊት የ 7000 (ሰባት ሺ) ዘመን ልፋቷ ታሰበ፡፡ ተወደደች ፡፡ እግዚአብሄር ወደዳት ባለድል ሆነች፡፡

ስማ የሰው ዘር !! ኢትዮጵያ በመንፈሱም በስጋውም ዓለምን የምትመራ፣ የምትገዛ ሆና በልዑል እግዚአብሄር ተሾመች !! እንደ ፀሀይ የሚያበሩ የእምነት አርበኞቿ ተቀቡ ! ተሾሙ ! በአምላካቸው ተወደዱ !!

ደምህን አዝርተህ፣ እምባህን እረጭተህ ፣ በጉልበትህ ተንበርክከህ፣ ቅጣትህንና ፍርድህን ተቀብለህ ለምህረት የተረፍከው ትውልድ ብቻ እጅህን ለኢትዮጵያ ትሰጣለህ፡፡ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ታያለህ ! ለዚችው ለተባረከች ምድር ትገብራለህ ! የሰረዊት ጌታ እግዚአብሄር ይህን ያደርጋል ! እወቅ የሰው ዘር ! ጌታ በከበረው ስሙ ምሏል፡፡ እኛም የታመንን ባሮቹ የውሳኔውን ማህተም ጨብጠናል፡፡ አስፈጻሚውም ከደጅህ ቆሟል፡፡ እንደ ንስር ዙሪያህን ይዞራል፤ አታመልጥም መሸሸጊያም የለም፡፡

በሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ስም ፤ በእመቤቴ ድንግል ማሪያም ስም አረጋግጥላችኋለሁ፡፡ ተፈጸመ ! ተከደነ !

ትንቢተ ኢሳኢያስ ም ፡ 62

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ

አሃዱ አምላክ አሜን

የሰራዊት ጌታ ስሙ ይባረክ !!!

በኢትዮጵያ ምድር ላላችሁ ከኢትዮጵያም ውጭ ላላችሁ ዜግነታችሁን እምነታችሁን ያልጣላችሁ ወገኖቼ በሙሉ ! ይህ በህይወታችሁ በአገራችሁ በኑሮአችሁ በዘራችሁ በሃብታችሁ ሁሉ ወሳኝ ሆነውን የአምላካችንን ፍርድና የመጨረሻው የቅጣት አመጣጥና የማዳኑን ውሳኔ ከዚህ ቢታች ባለው የመጨረሻው መልእክት እንድታነቡና ለሁሉም ወገናችሁም ሆነ ለሰው ዘር በሙሉ እንድታደርሱ በፈጠሪ ስም እጠይቃችኋለሁ፡፡

ትን ኢስኢያስ መፅ - 18

ይህ መልእክት እንደጉዳያቸውና በህይወታቸው ወሳኝ ጊዜ ላይ መድረሳቸውን ለተገነዘቡ የፈጣሪም ተግሳጽ ለሚያስደነግጣቸው ወደንስሃ ለሚመልሳቸው (እንደ ነነዌ ህዝብ ፈጥነው ለሚመለሱ መዳኛቸው ሲሆን) ለሚንቀው ለሚተቸው ለሚያንጓጥጠው ደርሶ አዋቂ ነኝ ብሎ ለሚመጻደቀው የትችትና የአሽሙር ምላሱን ለሚያስቀድመው ፤ ተውት ለሞት ልጅ አንዴ ለታወረ ምንም ቢሉት አይመለስም ፡፡ ፈጣሪያችን ከነ ክብሩ እንኳ ወርዶ ቢያናግረው አይሰማም፡፡ ለእሳት የተጻፈ ለእሳት ነው፡፡ የኢትዮጵያንና የአለምን መልካም አያይም ! ከመጪው የበረከት ዘመን አይደርስም ! ስለዚህ ለሰው በሙሉ በየትኛውም አለም በትኑ ! የፍርድ ቃል ነው ! አድርሱ ! አውቆ ይዳን ! አውቆ ይለቅ ማሳወቅ ብቻ ነው የኛ ግዴታ !!

አፌ ጽድቅህን ሁሉ ግዜ ማዳንህን ይናገራል

በእግዚአብሄር ኃይል እገባለሁ አቤቱ ጽድቅህን ብቻ አስባለሁ

አምላኬ ከታናሽነቴ ጀምሮ አስተማርከኝ

እስከዛሬም ታምራትህን እናገራለሁ

እስካረጅም እስከሸመግልም ድረስ ለሚመጣው ትውልድም ሁሉ

ከንድህን ኃይልህንም ጽድቅህንም እስከነግር ድረስ አቤቱ አትተወኝ

መዝሙር ዳዊት 70 (71) 15 – 18

የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡ አገራችንን ኢትዮጵያን ፈጣሪያችንና አዳኛችን፤ ለእናቱ ለድንግል ማሪያም የበረከት ልጆች አድርጎ፣ ምድሪቱንም እኛንም የሰጠ ጌታ የተመሰገነ ይሁን፡፡ በአባታዊ ቅጣቱና ማስተማሩ በጸጋው እየሸፈነ ሰው እንድንሆን ለመከረን፣ ለመራን፣ ላኖረን፣ ለቸሩ ፈጣሪያችን ምስጋና ይድረስ፡፡ እግዚአብሄር አብ፣ እግዚአብሄር ወልድ፣ እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ፣ አሃዱ አምላክ የተመሰገነ ይሁን አሜን !!

የነበረ ያለ የሚኖር ከመኖር ወደ አለመኖር የሚለውጥ ካልነበረ ወደህያውነት የሚያመጣ ማንም በማይቀርበው ብርሃን ውስጥ ያለ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር የተመሰገነ ይሁን !!

የኢትዮጵያ ህዝብ አድምጠኝ ! አስተውል ! ሁሉም ነገር አበቃ የፍርድም ሰአት ደረሰ፡፡

የቀረችውም ትንሽ ጊዜ አለቀች፤ የመጨረሻው የፈጣሪያችን የአምላካችን መገለጫ

የፍርድ ሰአት ደረሰ !!

የወደደን በአለም ሁሉ ፊት ለከብሩ ሊያቆመን ከዘመናት ጀምሮ ሊያት ቅድመ አያቶቻቸው የከፈሉትን፣ የደከሙበትን፣ የታመኑለትን፣ ለኛ ለልጆቻቸው ሊከፍለን ለወደደው እግዚአብሄር አብ፣ እግዚአብሄር ወልድ፣ እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ ከዘለአለም እስከ ዘለአለም ምስጋና ይግባው፡፡

በፈጣሪ ፊት ለተወደደው የኢትዮጵያ ህዝብ !

በተዋህዶ እምነትህ የጸናህ ውርደትን መከራን የጠጣህ !

በድንግል ማርያም እናትነት ያመንክና በአማላጅነቷ በኢትዮጵያ ባለ ርስትነቷ ታምነህ ለቆምክ !

ውርደቱ ንቀቱ ማጣቱ መገፋቱና መጠላቱ መገደሉ መገረፉ መታሰሩ ሁሉ ሳይበግርህ በፈጣሪህ ታምነህ ቆመህ እንባህን ላፈሰስክ ወገኔ ሰላም ይብዛልህ፤ ደምና አጥንትህን ለገበርከው የእግዚአብሔር ውድ የኔም ወንድም፤ ከዚች ቅድስት ምድር አብረን ለበቀልነው ወገኔ፤ በዱር በገደሉ ለምትንከራተተው የሰራዊት ጌታ የእምነት አርበኞች የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ጀግኖች !!

ከቤተክርስቲያን ተባራችሁ በተኩላ ለተሰደዳችሁ ሁሉ፤ የበይ ተመልካች ሆናችሁ በዘረኞች፣ በአመንዝሪዎች፣ በነፍስ ገዳዮች፣ የእምነት ካባ በለበሱ ቀጣፊዎች ለተረገጣችሁ፣ ቤት ንብረታችሁ ተነጥቆ፣ ትዳራችሁ ፈርሶ፣ ለልመና የተዳረጋችሁ ወገኖቼ !

እንደ ክረምት ሙጃ ሁሉን ቦታ ፈሰውና በቅለው ወፍረው ባበጡ የሙስሊም፣ የፕሮቴስታንት፣ የካቶሊክ፣ የጥንቆላ ሰረዊቶች ለተመታችሁ ለተዋረዳችሁ ወንድሞቼ እህቶቼ !

መንግስት ተብየው በኮለኮላቸው የሆድ አምላኪዎች ዘወትር ለምትገፋና ለምትጨነቁ በሙሉ !

ሰአት ደረሰ ፍርዳችሁን እንደፀሀይ የሚወጣው የሰራዊት ጌታ እነሆ በደጅህ ለፍርድ ቆሟል፡፡ ልትደሰቱ ህሊናችሁን ልታዘጋጁ ይገባል፡፡ ብዙ ወገኖቻችን መልካሙን ቀን ለማየት አየተመኙ የጌታ ፈቃድ አልሆነምና አልፈዋል፡፡ ለአገራቸው ለእምነታቸው ለህዝባቸው ተጨንቀው ተጠበው በጨለማው ገዢ ተረግጠው ተከፍተው ወደ ጌታችን እቅፍ ሄደዋል፡፡ ዛሬ በህይወት ያለነውም በዲያብሎስ እስራት ተጠፍረናል፡፡ ለረሃብና ለችግር፣ ለሞት ለመንከራተት፣ ለእስራት ለስደት ተመድበን በዚሁ ሰንሰለት ኖረናል፡፡ ብዙዎቻችን አምላካችን ዘገየ ብለን ተስፋ ቆርጠን ለጠላት እስከመንበረከክ ደርሰናል፡፡ እረኛ የሌለው ተቅበዝባዥ በጎች ሆነናል፡፡ የተኩላ እራትም እስከምንሆን ዘልቀናል፡፡ ወገኔ ! በዘርህ ተለይተህ ተረግጠሃል፣ በእምነትህ ተጠልተሃል፣ በአገርህ በጠላትነት ተፈርጀሃል፣ ይህችን አገር የማያውቋት ለጥፋቷ ለሚደክሙና ከእያት ቅድመ አያቶቻቸው ጀምረው ሲያጠፏት የኖሩ የሁሉ ነገር ባለቤት ሆነዋል፡፡ ሁሉንም ወርሰዋል፤ ሃብት ንብረት ሰበሰበዋል፤ ገንብተዋል፤ ወደ ነጩ ምድርም አፍልሰው አከማችተዋል፡፡ ማንም አይነካንም ብለው ራሳቸውን በግንብና በምሽግ ከልለው ተቀምጠዋል፡፡ በጦራቸው፣ በጀታቸው፣በታንካቸው በወታደሮቻቸው ታምነዋል፤ አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ቻይና፣ ህንድ በወዳጆቻቸው ታምነዋል፡፡

ወገኖቼ ኢትዮጵያውያን ! አገራችን መጠለያችን እንድትጠፋ እሷንም የሚወዱ ልጆቿ ከእምነታቸው እንዲከስሙ ተወስኖ መስራት ከተጀመረ ብዙ ዘመናትና አመታት አልፈዋል፡፡

አንድ ህዝብ፣ አንድ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነት፣ አንዲት አገር፣ አንዲት አረንጉአዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ብሎ ያመነና በዚህ የጸና ወገኔ ወንጀለኛ ነው፤ ስለሆነም ይሳደዳል ይገደላል ይታሰራል ቢዘረዝሩት ብዙ ነው፡፡ያለቀውና የደቀቀው ማንነትህ ይገልጸዋልና !!

ትግስቱ የማያልቅበት አምላክ አሁን ግን ትእግስቱ አለቀና አበቃ ! በስጋችንም ያመንናቸው ያደራጀናቸው ተበተኑ፡፡ ተስፋችን ጨለመ፤ በመሆኑም መታመኛ ጥበብ ሁሉ አለቀ፤ በመሆኑም ይህን የተመለከተው አምላካችን ትግስቱ ተሟጧል ! የማዳን ክንዱን አነሳ፤ ፍርዱን እንደጸሀይ ሊያወጣ ከሰማይ ማንጎዳጎድ ጀመረ !!

ተስፋህን አለምልም ወገኔ አባትህ የታመነው ጌታ ደርሱአል !!!

አንተ ባህርን በክንድህ አጸናሃት፤ አንተ የእባቦችን ራስ በውሃ ውስጥ ቀጠቀጥህ (ሰበርህ)

አንተ የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ

ለኢትዮጵያ ህዝቦችም ምግብን ሰጠሃቸው

መዝሙረ ደዊት 73 (74) 13 – 14

የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጥቃት

ከወዴት እንዴት ወዴት

በኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን መሸጋችሁ ከአለቃ እስከ ምንዝር ላላችሁ በሙሉ !!

የእግዚአብሔርን በጎች አርዳችኋል፣ በልታችኋል፣ ለአውሬ ሰጥታችኋል፣ ሸጣችኋል ፣ ለውጣችኋል፣ ለሆዳችሁ፣ ለከብራችሁ፣ ለገንዘባችሁ የእግዚአብሄርን እውነት ለውጣችኋል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ተሰብስባችሁ ዘወትር የጌታን ቁስል ትወጋላችሁ፡፡ በእመቤታችን ስም ትነግዳለችሁ፤ ታላግጣላችሁ፤ የፖለቲካ ሰራተኛ ሆናችሁ፤ የተሰጣችሁን መንፈሳዊ ስራና እረኝነት ለቄሳር ስራ ለውጣችኋል፡፡ ትገላላችሁ ታስገድላልችሁ፡፡

የአምላካችን ስጋው በሚፈተትበት ደሙ በሚፈስበት ቤተ ክርስቲያን በጎቹን ጠቦቶቹን ግልገሎቹን በሙሉ አርዳችሁ በልታችኋል ! ፍጹም ተኩላ ሁናችኋል፡፡

ህዝቅኤል ም ፡ 34

ስለዚህ አንድም አታመልጡም፤ ወዴትም መሸሻ የላችሁም፤ ፍጹም ትረገጣላችሁ ! የሰበሰባችሁትን እሳት ይበላዋል ! ለዘራችሁ ለስማችሁ ማረፊያ አታገኙም፤ እንደ ትቢያና አቡአራ ትበናለችሁ !!

ተሃድሶ ነኝ ! ጸጋ ነኝ ! ቅባት ነኝ ! እያላችሁ በእግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ ላይ ያላገጣችሁ የእመቤቴን ክብር ለመቀነስ የለፋችሁ፤ የጌታን ፍቅር ክፍያ ያሳነሳችሁ፤ የዲያብሎስ ልጆች ሆይ ! ፀሀይ ሲመታው እንደሚጠፋ ሙጃ ትደርቃላችሁ፤ ለእሳትም ትጣላላችሁ !!

እግዚአብሄር የታመኑ እረኞቹን መርጧል ! አዘጋጅቷል ! ቀብቷል ! ያፈረሳችሁትን ቤት ይገነባል፡፡ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ትታነጻለች፤ እንደ ገና እንደ ፀሀይ ታበራለች፡፡ አንተ ተኩላ፣ የሰይጣን ልጅ ትጠረጋለህ አንድህም አታመልጥም !!

ተዋህዶ ኦርቶዶክስ የእውነት እምነት ባለቤት እንጂ የተኩላዎች መሰብሰቢያ አትሆንም ! የመጀመሪያው ጽዳት በእግዚአብሄር ቤት ይጀምራል ! እሳት ይበረብርሀል፣ እሳት ያበጥርሃል፣ የዘራኸውን ታጭዳለህ !!

ያሳደዳችኋቸው ፣ ያሰራችኋቸው፣ የጨፈጨፋኋቸው፣ የገደላችኋቸው የእምነት አርበኞች፣ ይፋረዱአችኋል፤ በእሳት ያነደዳችሁት ገዳምና ቤተ ክርስቲያን እጅግ ውድ ዋጋ ያስከፍላችኋል !

ዛሬ ዲያብሎስን የምትመርቁና የምታወድሱ ዲያቆናትና ቄሶች፣ ባህታውያን፣ ጳጳሳት፣ ስጋችሁን አወፍራችሁ ምላሳችሁን አጣፍጣችሁ አለሃፍረት ላላችሁ ሁሉ የትም ገብታችሁ አታመልጡም፤ የከፋ፣ የበረታ ቅጣት ትቀበላላችሁ፡፡

የእግዚአብሄር ቤት ትታነጻለች . ከተኩላ፣ ከተባይ፣ ትጸዳለች፤ ታሪኩአ ይመለሳል፡፡ ክብሯ ይታደሳል፣ቅርሷ ይሰበሰባል፣የእምነት ባለሟሎችና አርበኞች ከተሳደዱበት፣ ከታሰሩበት፣ ከተጣሉበት፣በክብርና በሙላት ይመለሳሉ፤ ይፈወሳሉ፣ ይጠገናሉ፣ እንደ ጸሀይ ያበራሉ፡፡

እውነተኛ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ልጆች ይፈወሳሉ !ይጠገናሉ ! በለመለመው መስክ ያድራሉ ! በታመኑ እረኞች ይጠበቃሉ !!

ለፈጣሪ ታምናችሁ፣ በድንግል ማርም ጸንታችሁ፣ ለአገልግሎት ጸንታችሁ፣ ከንግድ ስራና ከሸመታ እርቃችሁ፣ ለቃሉ የምትተጉ አይዟችሁ፤ ዋጋችሁ በፈጣሪ እጅ ነው:: ትደምቃላችሁ ! ታበራላችሁ !!

ተዋህዶን እምነት ለስጋ ትርፋችሁ ያደረጋችሁ ወደ ንግድ ጣቢያነት ለለወጣችሁ ወዮላችሁ !!

ትንቢተ አሞጽ ም 2 ፡ ቁ 13 – 16

ስለጣፈጠው ምላሳችሁ በህዝብ ፊት የከበራችሁ በውስጣችሁ አመጽና ቅሚያ ለሞላባችሁ ልብና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ፍርዳችሁን እንደፀሀይ ያወጣዋል !

በሰው ፊት የከበረ በፈጣሪ ይናቃል:: በሰው የተናቀ በፈጣሪ ይከብራል:: ሰው እንደሚያይ ፈጣሪያችን አያይም፣ አይቶም አያውቅም:: እንደሰው የውጭን ገጽታን ፣ ውበትን፣ አለባበስን፣ አነጋገርን አያይም:: እሱ የሚፈትሸው ልብና ህሊናን ነው:: ፍርዱም የሚመሰረተው በዚህ መሰረት ነው:: በመሆኑም ብዙውን ሰዎች የወደዱትና ያጸደቁት ወይም የመረጡት ይወድቃል:: በተጻራሪው የናቁት ይጸድቃል::

ዳዊትን ከነትቢያ ያነሳ ፣ ሳሙኤል ብላቴናውን ከኤሊና ከከበሩ ልጆቹ ይልቅ ወዶ የመረጠ፣ አብርሃምን ከጣኦት አምላኪዎች መሃል መርጦ የወጣ፣ ሃዋርያትን ከየአሳ ማጥመጃ የመረጠ፣ ከተናቀው የቀረጥ ስራ የጠራ፣ የከበሩትን የህግ አወቂዎቹን አነ ገማልያንን ከከበረ ሙክራብ ላይ ያልጠራና ያልመረጠ እግዚአብሄር ሃሳቡ ከኛ ሃሳብ የተለየ ነው:: በኢትዮጵያችንም የሚሆነው ይኸው ነው::

ተናቁ በእውቀታቸውም፣በኑሮአቸውም፣ በሁሉም ነገራቸው እዚህ ግቡ የማይባሉ ተመረጡ !! ተቀብተው ታመኑ ! የእግዚአብሄር ምርጫ ነው:: ትቃወሙት ዘንድ ይቻላልን ! ምንስ ስለሆናቸሁ ! ሁሉንም ወደፊት ማየት የተሻለ ነው !!

ስለዚህ በመልካም ሰአት እግዚአብሔር ሊጎበኘን በቀረበበት ጊዜ በቤቱ የበቀሉ ጠማማና ወልጋዳዎች ይወገዳሉ ይጠረጋሉ ! ::

የዛሬው የተወህዶ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና እረኞች ስሙ አድምጡ ! ጊዜው አለቀ፤ የዘራችሁትን ማጨጃው ሰአት ደረሰ ! አጫጁም እነሆ በደጃችሁ ቆመ:: ፈጥነህ ውደቅ አታመልጥምና !

በፈጣሪ የታመኑትን የተወደዱትንና ለቃሉ የሚተጉትን፣ ከጳጳስ እስከ ዲያቆን ያሉትን በገዳማት በገጠር ቤተ ክርስቲያን በማስተማር ፣ በቅኔ፣ በድጉአ፣ በዜማ በአቋቋም፣ በተለያየ ትምህርተ ተወህዶ እምነት አንጸው በማውጣት የተሰማሩትን የእግዚአብሄር በጎችና እረኞች ለቅማችሁ አጥፍታችኋል:: በናንተ ቤት እግዚአብሔር አያይም ይመስላችኋል:: አሁን ወዴት ታመልጣለችሁ ! የፍጸሜአችሁ ቀን ደረሰ:: ስራችሁ ተከተላችሁ:: አታመልጡም የፈጣሪ ውሳኔ አርፏል ! የዘራችሁትን ታጭዳላችሁ::

እንሸሻለን፣ አናመልጣለን ብላችሁ አታስቡ፤ ይህ ድሮ ቀረ:: ከአሁን በኋላ ሰው አምልጦ የሚድነው ወደ ኢየሱስ መጥቶ በመጠለል ብቻ ነው:: ስለዚህ ሽሽት ወዴት ! እናንተ መሸሸጊያ ይሆናሉ ብላችሁ በስጋችሁ ያደራጅኋቸው እነባቢሎን (አሜሪካ)፣ እነአውሮፓ፣ ወይም ኤሽያ ፣ አረቢያም ሁሉም በእዚህም ጽዳት ይካሄዳል:: ምሽጉ የትጋ ነው ! ራሳችሁንና ስራችሁን ይዛችሁ በፈጣሪ እጅ ፍርዱን መጠበቅ ብቻ ነው:: ተጣምራችሁና እጅና ጓአንት ሆናችሁ አባራችኋቸው የምትሰሩላቸውን ሃይሎች እጣፈንታም ከናንተው ይከፋል እንጂ አይለይም:: ምሽግ የለም ! ሁሉም ተጭኖ መጥቶአል::

ኤርሚያስ 23 ፡ 1 – 6

ይድረሰ ! ለፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች

ልብ ብላችሁ አድምጡ !!

እናንተ የዘመኑ የጠላት መጠቀሚያዎች እጣ ፈንታችሁ እጅግ ያስደነግጣል:: በኢትዮጵያ የአገሪቱን የእምነት መሰረት በመናድ፣ ከማንም በላይ የደከማችሁ እናንተ ናችሁ:: አገራችን ኢትዮጵያ የጥፋት ተልእኮ እጅግ ተፈትናለች:: የዚችን አገር በእግዚአብሄር የታቀደ ስልታዊ አቀማመጥዋን ..... ይገባል:: ኢትዮጵያ ! በግዮን የተከበበች፣ በምድር ወገብ ሁሉ ብትዞሩ የማታገኙትን ከባህር ወለል በከፍታ ቦታ የተቀመጠች፣ የማንም ሃገር ስነ ምህዳር ያልጨበጠውን የተለየ የአየር ንብረት ..... የእንስሳት አይነት ያቀፈች፣ ያበቀለች ለሰው መኖሪያ ተስማሚነት ያላት አገር ነች:: ህዝቧም በመልካም ..... ነው:: በተፈጠሮው ፈጣሪ የቸረው አእምሮውም ለትምህርት የታነጸ ነው::

እናንተ ደግሞ ከዚሁ ህብረተ ሰብ ውስጥ በቅላችኋል፡፡ በስንዴ አረም እንደሚበቅል፣ በጨለመ ..... ሙጃ እንደሚበዛ፣ አገሪቱን ሸፍናችኋል፡፡ ከአጥፊው ስርአት ጋር ወግናችሁ አገሪቱን ታፈርሳላችሁ፤ ኢትዮጵያዊ ወኔንም ትሰልባላችሁ፤ እጅና እግሩን ትቀይዳላችሁ፤ አሁን ያለውን መንግስት አም..... የጠቀማችሁ የዲያብሎስ ሰራተኞች ናችሁ፡፡

እናንተ የምትንቁአት ይህች ቅድስት ሃገር የመቤታችን ድንግል ማሪያም አገርና ርስቷ ናት፤ በናንተ አፍ ሁሌ ትነቀፋለች፤ በናንተ የዲያብሎስ ውክልና ቅዱሳን መላእክት እነደ እቃ ዝቅ ተደርገው ይታያሉ፡፡

ምድርና ሰማይ የማይሸከሙትን አምላክ ፤ የሚባላ እሳት የሚፈጥረውን አምላክ ፤ በማህጸኗ የተሸከመች በነፍሷ ያሳለፈች፣ ደሟን የለገሰች እናት በናንተ ትነቀፋለች፤ ትሰደባለች፣ ዝቅ ተደርጋም ትታያለች፡፡

የሷን ክብር ለ2000(ለሁለት ሺ) ዘመን አክብራ፣ አቅፋ፣ ተባርካበት፣ ተወዳበት፣የኖረችን ኦርቶዶክስን እምነት በናንተ ዘመቻ ተመታለች፡፡ በሰርጎ ገቦቻችሁም ትታመሳለች፡፡ ቀንን፣ ወርን፣ አመትን ሁሉ ባለማቋረጥ እንደ ጅረት በሚፈሰው የምስጋና ዜማዋ ፣ ቅዳሴና ማህሌት አምላክን፣ እናቱ ድንግል ማሪያምን፣ የጌታን ባለሟሎች አክብራ የምታመሰግን ተዋህዶን ልታፈርሱ ከዘመታችሁ በኋላ እድሜያችሁም የሚለካው ከጽንሰታችሁ እስከአሁን እድገታችሁ በሰራችሁት አመጽ ነው፡፡

የትኛው የእምነት ተቋም ነው ! በዘመን ርቀትም ሆነ፣ለእምነት ጸንቶ መቆምን፣ በእጁ ማለፍን ያየ ! ያለ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነትስ ይህን የፈጸመ የሚፈጽምስ የት ነው ያለው ! የዘመኑ የዲያብሎስ መጠቀሚያዎች አድምጡ ! ማንስ አክብሮ ያኖረውን የእግዚአብሄር ቃል ትነሳላችሁ !

እንደ አርምኒኤም ጠል የሚንጠባጠበውን አንደ ምንጭ ውሃ በሚፈሰው የቅኔ ፣ የማህሌት ..... ፈጣሪዋን ያለማቋረጥ የምታመሰግን ተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነትን የሚመስል እስቲ አምጡ !

በተግባርም ደሃ የሚጠለልባት ! ቢከፋው ! የሚገድምባት እድሜውን ለፈጣሪው ለሚያስገዛባት ስጋን በጾም ለማድከም ከ 365 ቀኖች 2/3ኛውን ለጾም በመመደብ የስጋ ጉልምስናን ለመንፈስ እንዲገዛ በገነ.... መንፈሳዊ ስርዐት ያሰረጸች ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ናት፡፡

እናንተም ካቶሊኩም እስላሉም እምነት አለኝ ፈጠርኩ የሚል ሁሉ በዚች ተዋህዶ እምነት ላይ ጦሩን ሰብቆ አናንቆ መንፈሳዊና ስጋዊ ስብራት አድርሶ ለዘመቻው በዲያብሎስ ተወድሶ ኖሯል ኖራችኋል፡፡

ዛሬ ግን አበቃ ! በሰፈርከው ቁና አስር ዙር ሰፍሬ እጠርግሃለሁ፡፡ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ፣ እመቤታችን የድንግል ማሪያም ልጅና የደሙን ማህተም የጨበጥኩ፣ የታመኑት የተወደድኩት የልኡል ባለሟሎች ሚካኤልና ገብርኤል ለሁሉም ፈጥነው የሚደርሱልኝ፣ በእሳት ቅጥር አጥረው ፣ የሚጠብቁኝ የታመንኩ ወዳጆቸው ነኝ በዚህም የምመካ ነኝ፡፡ የአምላኬን ትእዛዝ ፣ የእመቤቴን ትዕዛዝ ፣ የወዳጆቼን ትዕዛዝ ልፈጽም ላስፈጽም የቆምኩ የልዑል ባሪያ ነኝ ከደፈራችሁ ጠብቁኝ ሂሳቡን እናወራርዳለን ይህን አትጠራጠሩ ምህረት ከኔ አታስቡ፡፡ ከስንዴ አረም እንደሚነቀል ከኢትዮጵያ ምድር እናንተንና ስራችሁን አሻራችሁን ማጥፋትና መጥረግ ዋናው ስራዬ ነው ! የምኖረው ለዚሁ ነው፡፡ ጊዜው አልቋል እኔም አጠንብህ ነኝ ፤ ከመሃልህ አለሁ« አኔ ብቻ አይደለሁም፡፡ የልዑል ባሪያዎችና የታመኑ ልጆች የደሙን ማህተብ የጨበጡ በመሃልህ ቆመዋል፡፡ ለአይናችሁ አንሞላም ውዳቂዎች ነን፣ በስጋችን የነለመስን ነን፡፡ በእምነታችን ቸሩ ፈጣሪያችን በጸጋውና በእሳት አጥሮ የሚጠብቀን ነን፡፡ ሁልህም ተሰናድተህና ወገብህን ታጥቀህ ጠብቀን ! የታመንከበትን ሁሉን እናየዋለን እንደጭስም ሲተን አናየዋለን አብረህም ትበናለህ ፍየልንና በግን አንድ ላይ የምናግድ አይደለንም፤ የተጠራነው ለበጎች እረኝነት ብቻ ነው፡፡ የምንታመነው ለእግዚአብሔር ህዝቦች ነው፡፡ ጠላትን የሚሸከም ጫንቃ የለንም !!

ሕዝቅኤል 13 ፡ 17 – 23

በእስልምና እምነት ውስጥ ላላችሁ ሁሉ !!

የእግዚአብሄርን ህዝብ ጨፍጭፎ ፣ ቤቱን አፍርሶ፣ በከፋ ጥላቻ ተሞልቶ፣ በህዝበ ክርስቲያን ላይ ዘምቶ፣ መኖር ይቻላል ብላችሁ እጅግ ብዙ ርቃችሁ ሄዳችኋል ! እስካሁንም እየሄዳችሁ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ምድር በቅንነትና በየዋህነት ብትስተናገዱ ስር ሰድዳችሁ እንግድነትን ረስታችሁ፣ ይህን ህይወት የሌለበትን እምነታችሁን በቅድስት ምድራችን ዘርታችሁ የአገሪቱን ከተማና ገጠር የጥቅም አውታራችሁ አድርጋችሁ ፣ ተዋልዳችሁ ከብራችሁ፣ ቤት ንብረት ገንብታችሁ፣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ሜዳ ላይ ወርውራችሁ፣ ንብረቱን ወራችሁ፣ ተቀምጣችኋል፡፡ ይህም አልበቃችሁ የበዙ የእግዚአብሔርን ህዝብ ገድላችኋል ! እጅግ ብዙ ንጹህ ደምም አፍሳችኋል፡፡ ትክክል እንደሰራ እንደባለመብትም ትፎክራላችሁ፡፡ በገዛ ሃገሩ በእምነቱ የተገፋው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የእግዚአብሄርን ፍርድ ሲጠብቅ ቆየ፡፡ ያለው የጥፋት አስተዳደር ደግፎአችሁ አድራጊ ፈጣሪ ሆናችኋል፡፡ በአለም ላይ የሚታየው እልቂት በእናንተው የጥፋት መምህሮች የተቀየሰ ነው፡፡ በገዛ ወገናችሁ ሞት ፈርዳችሁ ! አንዱ አክራሪ ! ሌላው አላሊ ! አንዱ ሱኒ ሌለው ሺያት! እነዚሁም ዋቢያ በሚልና በተለያየ የጥፋት መመሪያ ታጥቃችሁ ያለቃችሁን የዲያብሎስን ስራ በግንባር ቀደምትነት በመፈጸም ላይ ናችሁ፡፡ አንድ ሺ አራት መቶ ሰማንያ ሁለት አመት የሳለፈው

የጥፋት ተልእኳችሁ ይደመሰሳል። ከነምልክቱም ይመረጋል። እናንተ በፈጣሪ ፈቃድና አሳብ ላይ የዘመታችሁ ናችሁ ! የእውነት ጠላቶች ናችሁ ! ስለሆነም ፍርዳችሁን ጌታ እንደ ፀሀይ አውጥቶታል። እንደሌላው ጣኦት አምላኪ ሁሉ የእናንተም እጣ ፈንታ ከምድረ ገጽ መጠረግ ብቻ ነው።

በኢትጵያ ምድር እንኳን ልትኖሩበት ምልክታችሁም አይገኝም። አይታይምም። የሚሆነው ይህ ነው።

አንዲት ሃገር ታላቋ ኢትዮጵያ ትታነጻለች ትቆማለች !!

አንድ ህዝብ ታላቁና የተወደደው በፈጣሪ የታመነው የኢትዮጵያ ህዝብ በአለም ሁሉ ፊት ይነግሳል፤ እንደ ለመለመ ወይራ ያብባል !!

አንዲት እምነት ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ብቻ እንደ ፀሀይ የምታበራ ምድር ትሆናለች !!

አለምን ሁሉ አንቀጥቅጠውና በፈጣሪ ህግ አስረው የሚገዙ የእግዚአብሄር የታመኑ ልጆችና ባሮች ተዋህዶ ኦርቶዶክስ አርበኞች የሚነግሱባት ኢትዮጵያን ታያላችሁ ! ይህንን የሚያዩት ደግሞ ከውስጣችሁ ተጸጽተው የሚመለሱ ብቻ ይሆናሉ። ለምስክርነትም ይቆማሉ።

ስለዚህ በተመካችሁበት ሆናችሁ ጠብቁ። ያስተዋላችሁ ደግሞ ለእውነተኞይቱ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ እምነት ነገ ዛሬ ሳትሉ ሳይጨልምባችሁ እጃችሁን ስጡ ! በፈጣሪ እጅ ውደቁ ! ሌላ ማድረግ የምትችሉት የለም። ከሁለት አንዱን መምረጥ ብቻ ነው። የዘለአለምን ሞትና የስጋንም ሞት። ወይም ደግሞ የዘለአለምን ህይወትና በስጋም መባረክን ! እንዲሁም እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን! ከዚህ ውጭ ሌላ መንገድ የለም። እኛም ትዕዛዙን ለመፈጸም ከአምላካችን ብርሃን ኃይላት ጋር ቆመናል። ጨለማ ይጠፋል ብርሃን ይነግሳል፤ አንዱ ባለበት ሌላው ተጻራሪ አይኖርም!!

ልብ ብለህ አድምጥ ! የሰው ዘር በሙሉ !!!

እግዚአብሄር አብ አባታችን፣ እግዚአብሄር ወልድ አባታችን፣ እግዚአብሄር መንፈስ ቅዱስ አባታችን፣ አንድ አምላክ አባታችን ስሙ ይባረክ ! አሜን !

ከረጅም ጊዜ ትግስት በኋላ ቅን ፍርዱን እንደ ጸሀይ ያወጣ አምላካችን የተመሰገነ ይሁን። ስሙ ይባረክ !

አምላካችን 2000 (ሁለት ሺ) የምህረት ዘመን ለገሰ፤ አመጻችንን ከደነ፣ ሸፈነ፣ ታገሰ። የታመኑ ልጆቹ .....ደሉ፣ ለአውሬ ሲጣሉ የመጫወቻ ሜዳ ማድመቂያና በነሱ ስቀይና ሞት መደሰት እንደመዝናኛ ሆኖ ሲያልፍ (በሮም ያለው ኮላስየስ ስታዲዮም የቆመ ምስክር ነው) ጌታ ዝም አለ። ከአፉ የወጣውን ቃል የሚያውቅ ጌታ ጽዋው እስኪሞላ ጠበቀ። አያት ቅድመ አያቶቻችሁ ቅምቅም አያቶቻችሁ ምንጅላቶቻችሁ በእግዚአብሄር በጎች ደም ሲንቦራጨቁ አገር ሲገነቡ ግዛት ሲያስፋፉ ፣ ሃብት ሲሰበስቡ በአመጻቸው ሲገፉበት በመጠ....ት ታገሰ።

የቀድሞው እባብ ልጆች በአመጻቸው ገፉበት፣ አውነትን አጥፍተው፣ ከጌታ የወጣውን ቃል አጣመው፣ የራሳቸውን ስጋ ፍላጎት ጨምረው፣ ቀንሰው፣እውነት የሚመሰክሩትን ንቀው፣ አጥፍተው አሳደው፤ በምትኩ የዲያድሎስን ድርሰት አስተማሩ። እናንተም ልጆቻቸው ከነሱ አብልጣችሁ ተገበራችሁ፣ በዘመናዊ ጥበብና ዘዴ በአለም ሁሉ በተናችሁ። አረም ከተመቸው እህልን ይውጣል ፣ የጨለማ ጊዜ ለሴባና ለቀጣፊ ይመቻል። በመሆኑም 2000 ሺ ዘመን የዘለቀ የጨለማ ስራችሁ፣ አቅማችሁና እውቀታችሁ እስከፈቀደ ድረስ፣ የዲያብሎስም እውቀቱ እስከ ደረሰበት ድረስ፣ የጥፋት ስራችሁን፣ ይበጀናል ያላችሁትን ሁሉ ሰራችሁ ጨረሳችሁ። ዛሬ ግን በቃ፤ ዘመናችሁ ተደመደመ። የማያልፍ፣ የማያልቅ የመሰላችሁ ዘመን አለቀ። ታሪክ ወደ መሆን ትሸጋገራላችሁ።

ሴቶችና ዘመኑ። እንዲሁም መጻኢ እድልቸው !

በአሁኑ ወቅት በመላው አለም ጎልቶ የሚታየው የዲያብሎስ ዋናው የስራ መገለጫ ምንዝርና ነው። በአሁኑ ዘመን የምናየው ምንዝርና ፍጹም ልቅ የሆነና በምድራችን በየትኛውም ትውልድ ያልታየና ወደፊትም ፈጽሞ ይታያል ተብሎ የማይታሰብ ነው።

በዚህ የምንዝር ተግባር እጅግ በከፋ መልኩ ተዘፍቀውና ወድቀውበት የሚገኙት ሴቶች ናቸው። በመላው አለም ያለው ሙገሳ ፤ ውደሳ፣ ድርሰት ጽሁፍ፣ ፊልም፣ ዘፈን፣ ሆቴል ድርጅት፣ የውሃ ዳርቻ፣ የብስ፣ ባህር ሁሉም ተጨርሶ አልቆ ፤ የእግዚአብሄር ቤት ሳይቀር በምድር ላይ አንድም ክፍት ቦታ ሳይተው ሁሉም ምንዝርና ማስፋፊያ፣ ማደራጃ፣ ማስፈጸሚያ ወደሚከፋ ደረጃ ማሸጋገሪያ ሆኖአል። ይህ ሁሉ ፀሀይ የሞቀው እውነት ነው። በዚህ ምግባር ሴቶች ዋንኛውን ስፍራ ይዘዋል። ገላቸውን አራቁተው በጠራራ ፀሀይ በመዞር ለፍትወት ሁሉን ይጋብዛሉ። ሃፍረተ ስጋቸውን በማጋለጥ የተቃራኒን ጾታ የፍትወት ስሜት ለመቀስቀስ ከጧት እስከ ሌሊት ይደክማሉ። ዲሞክራሲ መብት ነው በሚል የዲያብሎስ ህግ በመመራት አካላቸውን ይሸጣሉ። መተዳደሪያ አድረገውታል። መሪዎች ታዋቂ ግለሰቦች በሙሉ የምንዝርናን ተግባር በመፈጸማቸው እንደ ነውር የሚሰማቸው አይደሉም።

በዲያብሎስ የተሾሙ ናቸውና ! ስለዚህ ምንዝርና የየእለቱ ተግባር ነው፡፡ ፈጣሪ አምላካችን አታመንዝር ያለውን ህግና ትዕዛዝ በመጣስ ከጧት አእስከ ማታ መፈጸም የተለመደ ተግባር ሆኖአል፡፡

ነውርን ከማድረግና ከመፈጸም ማፈር ቀርቶ በአምላካችን የተከለከለውን አታመንዝር የሚለውን አ..ስ እንደ ነውር ተቆጥሮአል፡፡ በትዳር የተወሰነች ገላዋን የሸፈነች ሴት እንደ ውዳቂና አላወቂ ያልሰለጠነች ተብላ ተቆጥራለች፡፡ የማያመነዝር ወንድም እንደ ጅል ከተቆጠረ ሰነበተ፡፡

ወንድና ወንድ፣ ሴትና ሴት በፈትወት ከተቃጠሉ፣ የሰዶምን ስራ በብዙ እጥፍ በልጠው ከተገኙ ቆየ፤ እንደውም እንደ መብት ተቆጥሮላቸዋል፡፡ ይጋባሉም፣ ቤተ ክርስቲያን እመራለሁ ፣ አስተምራለሁ፣ ምእመንን ወደ እውነት እመልሳለሁ የሚል ቄስ፣ ጳጳስ እራሱ ግብረ ሰዶማዊ ሆኖ ተገኘ፡፡ እንደ ትክክልም ተግባር በመቁጠር በአደባባይ ተከራከረበት፡፡

በአገሬ በኢትዮጵያ አጅግ የከፋ የምንዝርና ተግባር ለመፈጸም ፈጻሚውም ተመልካቹም ሁሉም የሚያየው ያልተሸፈነ የተፈቀደ ተግባር ሆኖአል፡፡

የኛ መንግስት ስለ ሰዶማውያን ሲጠየቅ የሰጠው መልስ፤ ህገ መንግስታዊ መብታቸው ነው፤ አንከለክልም የሚል ነበር፡፡ መልሶ እራሱን ከድርጊቱ አድናቂነት ለመሸፈን፤ ቤተ ክርሰቲያን ታስቁም እንጂ እኔን አያገባኝም ብሎ በተዘዋዋሪ ሳይሆን በግልጽ ይኸው ተግባር እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ሴቶች የተከለከለውን በወንድ ልብስ ማጌጥ፣ መብታችን ነው በሚል የሰይጣን ብሂል በመነዳት ማንም ሊከለክለን አይችልም ብለው በድርጊቱ ከተጠመዱ እጅግ ቆዩ፡፡ ከወንዱም በፍጹም የማይለዩ ሆነዋል፡፡ከሱሪውም አልፈው መላ ገላቸውን በማሳየት ከጠዋት እስከ ማታ ዝናብና ፀሀይን ሳይመርጡ ሲዞሩ ይስተዋላሉ፡፡

ኦሪት ዘዳግም ም ፡ 22 ፡ ቁ5

ምንዝርና ነውር መሆኑ ቀርቶ አለማመንዘር ነውር ሆነ፡፡ አንድም ሴት ከነ ክብርዋ መቆየትም ከናቀች ቆየች፤ ክብርዋን የትም መጣል መሰልጠን ሆነ፡፡ በምንም መለኪያ በምንም መንገድ ለዚህ አመንዛሪና አንጓጣጭ ትውልድ መራራት እጅግ ይከብዳል፡፡እርኩሰታቸሁ አለምን አጥለቅልቆታል፡፡ በመሆኑም ከአባታችሁ ዳያቢሎስ ጋ ትጠረጋላችሁ፡፡ መልካሙንና ጽድቅን ብትሰራ ላንተ እንጂ ለፈጣሪ ምን ይጠቅመዋል! ምንስ ይጨምርልታል! ክፉ ብትሰራ እምትጎዳው እራስህን እንጂ ከፈጣሪ ክብር ምንስ እምትቀንሰው አለ! ስለዚህ ቁጥርህ በረከተ አልበረከተ ምንም ትርጉም የለውም፡፡ እንደ ኖህ ዘመን ትጠረጋለህ! አስታውስ! እጣህ እንደ ሰዶማዊያን ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ምድር ፤ ከናንተ የበለጠ የቅጣት በትር የሚያርፍበት የለም፡፡ መሸሸጊያም የለም! ምንነው ባልተፈጠርኩ የምትልበት ሰአት መጥቷል አጥፊአችሁ በየደጃችሁ ቆሞአል፡፡ ፈጣሪም ምድርም ተፍታኋለች፡፡

በምንዝርና፣ በውሸት፣ በጭካኔ፣በሌብነት፣በነፍሰ ገዳይነት፣ የተበከልክ ስራህም ያደረግህ ወንድም ሆንክ ሴት በፈጣሪ እሳት ትበጠራለህ፡፡ ማንም የሚያመልጥ የለም፡፡ መልካሙን ዘመን የሚያዩት በፈጣሪአቸው ህግ የተመሩ፣የኖሩ፣ ሲወቀሱ ፈጥነዉ ንስሃ የገቡ ብቻ ናቸዉ፡፡ ከጥፋት ወደ ጥፋት ለምትነጉደዉ፣ ተግሳጽና ምክር ለናቅከዉ፣ ለጠፋኸዉ ትውልድ፣ የጨለማ ልጅ ከጨለመ ስራዉ ጋር ጨለማው ሲጠረግ አብሮ ይወገዳል፡፡ የብርሃን ልጅ ደግሞ በብርሃን አለም ተባርኮ ይኖራል፡፡

በምንዝርና፣ በክህደት፣ በውሸት፣ በንጥቂያ፣ በቅሚያ፣ በግድያ፣ እናትና አባትን በማዋረድ፣ በስርቆት፣ በዚህ ሁሉ ተክነህ የዘለቅህ ሽማግሌ፣ ወጣት፣ ባልቴት፣ ሁልህም ትፈተሻለህ፣ ትበጠራለህ፣ ቀለህ ስትገኝ ለእሳት ትጣላለህ፡፡ የሚያመልጠዉ ደግሞ አንተ የናቅከዉ፣ ውዳቂ ያደረግከዉ፣ አንተ ከምትሰራዉ ወንጀል የራቀና ከልቡ ንስሃ የገባ ይሆናል፡፡ በምንም ዘዴ የማታመልጠዉን
የብርሃን ፍርድ ትቀበላለህ፡፡ ሁሉም በደጅህ ነዉ፡፡ ጊዜዉም ተፈጽሞአል፡፡

ምሳሌ ም 6 ፡ 26 – 35 ወደ ሮሜ ሰዎች ምእ ፡ 1

ህዝቅኤል ምእ 16 ፡ 31 – 34 ምሳሌ ምእ ፡ 7

በዉጪ ስላሉ ኢትዮጵያዉያን!!

በዉጪ በስደት ያላችሁ ወገኖቻችን አገራችሁን እየወደዳችሁ በችግር የሄዳችሁ የችግር ምልክት የሆነዉን ዜግነታችሁን ያልጣላችሁ ያልለወጣችሁ የፈጣሪዬና የምዩ ልጆች ጊዜዉ ስለመሸ እራሳችሁን እንደ ሎጥ ከሰዶም ከተማ ለማስመለጥ ከፈጣሪአችሁ ጋር በብርቱ ተነጋገሩ፤ እመቤቴን ጠይቁ፤ ጊዜም አታጥፉ! አጥፊዉ በመላዉ አለም በሁሉም ስፍራ ታዞ በደጅ ቆሞአልና!!

የአገራችሁ ትንሳኤ እነሆ እንደ ፀሀይ ሊያበራ ነዉ፡፡ የምዩ ልጆች እውነተኛ ተዋህዶ አርቶዶክሶች አይዞአችህ አምላካችሁ ደርሶአል፡፡ በደጅም ቆሞአል ራሳችሁን አዘጋጁ ጊዜ የለም! አትዘናጉ ተፈጽሞአል፡፡ በሌላ አኩአያ ኢትዮጵያዊ የነበርክ ኢትዮጵያዊነትህን የናቅህ ዜግነትህን የለወጥህ ለፍርፋሪ የሸጥህ ብኩርናውን ለምስር ወጥ እንደ ሸጠዉ ኤሳዉ ክብርህንና ብኩርናህን ለለወጥህ ምንዝርናን የለመድህ ከአህያ የዋለች ጊደር ፈስ ትማራለች እንደተባለ ምንዝርናን፣ ዉሸትን፣ ንቀትን፣ስስትን፣የተማርክ ተዋህዶ

እምነትህን ንቀህ ከፈረንጅና ከአረብ እምነት የቃረምከና የተቀበልክ፣ መንገድህ ያድንህ፣ ያመንክበት ይከልልህ ለካቶሊኩም፣ ለፕሮቴስታንቱም፣ ለእስላሙም፣ ለሂንዱም፣ ለቡዲሂዝሙም ተከታይ ሁሉ የሚጠብቀው ሁሉ ላንተም ይጠብቅሃል ተዝጋጅተህ ጠብቅ!!

ህዝቅኤል ምእ ፡ 14 ፡ 12 – 20 ዘጸአት ምእ ፡ 12 ፡ 21 - 28

ኢሳኢያስ ምእ ፡ 40 ፡ 6 - 8 ኢሳኢያስ ምእ ፡ 57 ፡ 11 - 13

ከሊቅ እስከ ደቂቅ ላለህ ወገኔ በሙሉ!!

ሁሉም የሚመዘንበት የሚዳኝበት፣ የሚለይበት፣ ሰአት ተፈጽሞአል የሚቀረው ስንዴውን ወደ ጎተራ እንክርዳዱን ለእሳት መስጠት ብቻ ነዉ:: ሽማግሌ ባልቴት፣ ጎልማሳ ጎልማሲት፣ ወጣት ሴት ወንድ ሁልህም ልብና ኩላሊትን በሚመረምር አምላክ ተለይተሃል! ለምህረት የተጻፈዉ በግንባሩ ምልክት በስውር ተደርጎበታል:: ምህረትን የማያገኘዉ (ለእሳት የተጻፈው) ምልክት አልባ ነው::

በስውር የታተመው ምልክት የጨበጥህና ያልጨበጥህ መሆንህን የሚለዩህ ቅዱሳን መላእክት ስለሚያውቁህ! የሌለውን ለእሳት ያለውን ወደእረፍትና ወደምህረት የምታውቀው ደግሞ ስትድን ከመአቱ ስትተርፍ ብቻ ነው:: መዳንህንም በዚህ ታረጋግጣለህ:: ከአጠገብህ ያለችው ያለው ሲሸኙ ምልክት አልባ መሆናቸዉን ታዉቃለህ ትረዳለህ::

እኔ መሪ ነኝ፣ እኔ ሚኒስቴር ነኝ ፣እኔ የእምነት መሪ ነኝ፣ የጦር አለቃ ነኝ፣ ባለኒዩክለርም፣ ባለጠብመንጃ ብትሆን የአለም መሪም ሁን፣ የአጥፊዉ ጋሻ ጃግሬ ስለነበርክ፣ አለቃና ምንዝር ስለሆንክ፣ የዘር ሹመኛ ተጠቃሚ፣ የዘር ፈራጅ ስለነበርክ ምንም ከምንም የሚያድንህ የለም:: ሁሉም የአለም ገጽታ በሙሉ በሞት ይፈተሻል:: የሚያድንህ የልብህ ቅንነት እምነትህና ስራህ ብቻ ነዉ::

የሰበሰብከዉ ሃብት፣ ንብረት፣ በምህረት ለታሰቡት ይቀራል:: አንተ እንደዘራኸው ታጭዳለህ፣ ፈጣሪህን .... እንደ አምላክ ቆጥረህ የተከለልከዉ በዘረኛ ገዢ ጉያ ነው:: እሱ ስለሚሄድ አንተስ ወዴት ትቀራለህ!! አብረህ ትጓዘለህ:: የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም እንደሚባለው ለሆድህም ሆነ ላመንክበት አላማ ያዉ ከሃዲ የእግዚአብሄር አገር የወገን ጠላትነህ፤ ስለሆነም ስፍራህ መቃብር ብቻ ነው:: እንደ ስራህ መጠን ይከፈልሃል::የማንም ገዢ አያመልጥም:: ራሱንም ሆነ አንተንም አያድንም:: ስለዚህ ከፊትህ የመጣዉን የፈጣሪ በትር ሳያበጥር እንደማይመለስ ተረድተህ ታጥቀህ ጠብቅ! የታዘዘዉ አጥፊህ በየደጅህ ቆሞአልና::

ይህንን መልእክት ስታነብ እንደለመድከው የስጋ ብልጠትና የፖለቲካ ክህሎት ያዋጣኛል ብለህ እንዳታስብ:: መከራህም ከሚያከብደው በቀር የሚፈይደዉ የለም::

አለም ገና ከእንቅልፉ አልነቃም፤ በመጣበትም ቁጣ ፈጽሞ አልደነገጠም ሁሌም እንደሚያስበዉ በእዉቀት በእረዳ ተረዳዳ በገንዘብ እወጣዋለሁ ብሎ ያምናል::

በምድር መንቀጥቀጥ፣ በንርፍ፣ በማእበል፣ በሙቀት፣ በረሃብ ሲመታ ኮንፈረንስ ያደራጃል፣ ሳይንሳዊ ዘዴ ይተልማል፣ የእርዳታ ድርጅት ይሰይማል ደረስኩ ይላል:: ይሄ ሁሉ ይቆማል አይረዳም ለራሱ የሚሰጠዉን ካራና በትር ስለማይቋቋም አንዱ ላንዱ የሚረዳዳበት ወቅት ይጠፋል:: ሁሉም እንደ ስራው በመጣው ጥፋት ይጠረጋል:: እንደ ጪስም ይተናል:: ምድራችን እዉነትን በማያዉቁ አመጸኞችና ወንጀለኞች የዲያቢሎስ ልጆች ስለተሞላች በግድ መጽዳት አለባት:: ለቅዱሳንም የተመቻች የበረከት ምድር ልትሆን ይገባል! ስለሆነም ይኸዉ የፈጣሪ ፈቃድ ይፈጸማል::

በኢትዮጵያ የሚደርሰው የሚፈጸመው ሁሉ እነሆ ይመጣል! እግዚአብሄር የቀባቸው በምድሪቱ ላይ ሲነግሱ ያኔ ብቻ የአረፍት ጅማሮ ይሆናል:: ይህ እስኪሆን ግን አለም አይታ የማታውቀውን ጥፋትና ውድመት ታስተናግዳለች በዚህን ጊዜ ሁሉም የሚጮኸው የፈጣሪ ቁጣ እንዲቆምለት ብቻ ነው:: ያ ደግሞ የሚሆነው የታዘዘው ሁሉ ሲፈጸም የእግዚአብሄርም ህዝቦች ነጻ ሲወጡ ብቻ ነው::

የታመኑ የፈጣሪ ልጆች በአለም ሁሉ ፊት የሚያበራውን ከጌታ የተሰጣቸውን ስልጣን ሲያጸኑ! ሁሉም ሲንበረከክና በፈጣሪና ላከበራቸው ሲገዛ ብቻ ነው! ሰላም፣ በረከት፣ ቸርነት፣የሚሆነው ይኸው ሲሆን ብቻ ነው:: ይህ ደግሞ ከብዙ ጉዳት በህዋላ የሚፈጸም ነው:: ምክንያቱም የሰው ልጅ ትእቢቱንና አውቃለሁ ባይነቱን ቶሎ አይጥልምና!! አለም ሁሉ በታላቅ እንባና ጩኸት ይሞላል:: ከቁጣው ብርታት የተነሳ አለም ያለፈች እስኪመስል ድረስ ፤ አሁንም ደግሜ እለዋለሁ! በኢትዮጵያና በዙረያዋ ባሉ ተራሮች (ሀገሮች) ሁሉ የብርሃን ዙፋኑን የሚዘረጋው ጌታ ልጆቹን ከዙፋኑ ላይ ሲያስቀምጥ ብቻ ነው መስከን የሚጀምረው ከዚህ ውጪ የሚመጣ አንዳችም ነገር የለም::

እግዚአብሄር ለምህረት ያሰባቸው ክርስቲያን ሆኑ እስላም ሆኑ ካቶሊክ ሆኑ ሌላም ሆኑ ድርጅት ውስጥም ኖሩ አልኖሩ እምነት ይኑራቸው አይኑራቸው፤ ብቻ ልባቸው ቅን የዋህ ትሁትና ደግ ከሆኑ እውነትን የሚወዱ ከሆነና ፈጣሪን የሚፈልጉ ይሁኑ እንጂ! አምነውና ተጠምቀው በብርሃናዊቷ ተዋህዶ አርቶዶክስ ልጅነት ተባርከው በብርሃን ጎዳና ይገሰግሳሉ! የምህረትንም ዘመን ያያሉ ይኖሩበታልም::

የኢትዮጵያ ትንሳኤ!!

ወገኔ የኢትዮጵያ ህዝብ በፈጣሪህ እጅግ የተወደድክ ህዝብ እኮ ነህ እጅግ ላከበራት ለእናቱ ለእናታችን ለድንግል ማርያም ልጅ አድርጎ የሰጠህ ለማንም ያልሰጠውን በረከትና ህይወት ያዘዘልህ እኮ ነህ!! የእምዬ (የድንግል) ልጆች ለመሆኑ እንዲህ ለወደዳችሁ አምላክ ምን ትከፍላላችሁ!! አለምን ሁሉ ለእናንተ እንዲገዛ እንዲታዘዝ ወሰነ:: እስቲ ወገኔ አስተውል! ያለፉት ለዚች የተባረከች ምድር የደከሙት አባቶቻችንን ድካም ለ 7000 (ሰባት ሺ) ዘመን ሲመዝን፣ ሲለካ፣ሲመዘግብ ኖሮ ቃሉን በፍጹም የማያጥፍ ጌታ ለኔና ላንተ ላንቺ ብድራትን ሊከፍል መጣ!! ለመሆኑ ምንስ ትከፍለዋለህ!! ጌታ ሌላ አይጠይቅም ከልብህ የሚመነጨውን ምስጋና ብቻ ነው::

በፈጣሪ ፊት ያለህን ክብር አላወከውም! አሁን ግን ልታውቀው ይገባሃል:: በስራህ አይደለም የወደደህ አያት ቅድመ አያቶችህ በእምነታቸው ቆመው በጸጋው ያፈሱት በረከት ነው:: ለዚህም የትንሳኤ ዘመን ያደረሰህ የታመነ አምላካችን ሁሌም የታመነ ነው:: ከቃሉ የሚጨመር የሚቀነስ የለም::

አድምጥ ደስም ይበልህ!! በአለም የሚያበራ ክብር ለኢትዮጵያ ተሰቶአታል!! በበረከቱና በቸርነቱ በፍጹም ፍቅሩም የምትሞላው ኢትዮጵያ በእመቤቴ የእናትነት እቅፍ እና በረከት ታኖርሃለች:: ከእንግዲህ አገርህ ኢትዮጵያ ወደውርደት አትመለስም ለበረከት የታደልከው ወገኔ እንደ አሁኑ ከፉ ትውልድ ፈጣሪህን እንዳታስከፋው እነግርሃለሁ:: አሁን ቁጣውንም ጥፋቱንም ታየዋለህና ከፈጣሪህ ፈቀቅ እንዳትል ከዚህ ጥፋት በኃዋላ በበረከቱና በቸርነቱ ብዛት ደስታህ እጅግ ስለሚበዛ በስጋ ምቾት ተጠልፈህ ከፍቅሩና ከቸረህ ጸጋው እንዳትኮበልል ተጠንቀቅ!!

የተባረከው ወገኔ አንተ መልካሙን ታያለህ ልጆችህም እንዲያዩና ለትውልድ እንዲያዘልቁ አብረን ታምነንና ለአምላካችን ቃልና ትእዛዙ ተግተን አገራችን በፈጣሪ ፊት እንደታመንች፣ እንደተወደደች፣ እንድትዘልቅ የሚያደርገውን ስራ እንስራ!!

በፍቅሩ ኑሩ የሚጠላውን ጥላ፣ የሚወደውን ውደድ አሁን የምታየውን ዲያቢሎስ የዘራውን አመጽና የጥፋት አዝመራ ከምድርህ አጥፋ፣ እውነትን ብቻ አንግስ:: ሙሴ በእስራኤላውያን ከህደት ሲበሳጭ እግዚአብሄር ያለውን ልታስብ ይገባሃል:: ጌታ እንዲህ ነበር ያለው፣ ሙሴ ባሪያው ይህንን ልቡ ጠማማ ህዝብ ላጥፋው ተወኝ አንተንም ለታላቅ ህዝብ መሪ ላድርግህ ነው ያለው፣ ያ ታላቅ ህዝብ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ሙሴ አስተዳደርን የተማረው ከኢትዮጵያዊው የሚስቱ አባት ከዮቶር ነበር:: ኢትዮጵያ በህገ ልቦና፣ በህገ ኦሪት፣ ዛሬም በህገ ወንጌል ያለውን ስርአት ሳታፋልስ ትውፊቱን ጠብቃ መጥታለች:: እግዚአብሄር አምላካችን በባሮቹ በኩል ያስተላለፈውን ቅዱስ ቃሉን፣ በጥንቃቄ ጠብቃ ላንተ ለዛሬው ትውልድ አድርሳለች:: ሌላው የናቀውን የጣለውን የደለዘውን የቀነሰውን ተግባር ሳትከተል በትክክል እንደነበር እንደቃሉ ጠብቃ አኑራለች::

ከአለም ሁሉ በሚለየው የእምነት ስርአትዋ ዛሬም ሁሌም እንደ ጠል በሚንጠባጠብና እንደ ምንጭ ውሃ በሚንቆረቆር ዜማዋ ፈጣሪን ታመሰግናለች::

ታላላቅ መሪዎችን እግዚአብሄር ሰጥቶአት ነበር:: እነ ካሌብን፣ እነ ኢዛናን፣እነ አብርሃ ወአጽብሃ፣ እነላሊበላን እነ ዘርአያእቆብን ወዘተ... በእምነቱም በስጋውም አገዛዛቸው የገነኑትን አሳልፋለች:: ግዛትዋም እጅግ የሰፋና እስከ የመን የዘለቀ ነበር:: በየዘመኑ የተነሱ ጠላቶች ሲቀንስዋት ሲሸርፍዋት መጡ፣ መሪዎቹም በታሪክ እያነሱ መጡ፣ የቅርቡን ብናነሳ ከዘመነ መሳፈንት ጀምሮ በኢትዮጵያ ታሪክ በድንበር ጉዳይ ብዙ የተወሳሰበ ሁኔታ ተፈጥሮና እስከዘሬ ተወሳስቦ እንደቀጠለ እናያለን:: በታሪክ ያነሱና አገራቸውን እየሸረፉ ለጠላት በመስጠት ለስልጣናቸው መደላደል ብቻ የሚደክሙ መሪዎች እነሆ ቆመን እያየን ነው! የታሪክ ድንቸነት ፈጽሞ የማያማቸው ናቸው::

ይሁንና ወገኔ አትጨነቅበት ጠላት በየአቅጣጫው በቃኘው በነደፈው አካሄድ ሁሉ ኢትዮጵያን ከምድረ ገጽ አጥፍቶአል:: ዛሬም የሚችለውን እያደረገ ነው:: ይሁንና ፈጣሪ ሁለንተናዊ ጥበቃ ስላደረገ እዚህ ደርሳለች::

ከአሁን በህዋላ ግን ይህ ታሪክ ይቀየራል:: ሃፍረትም መሸማቀቅም ለጠላቶች ይሆናል:: የጠበበው የተሸረፈው ወደነበረበት ብቻ ሳይሆን እጅግ በማትገምተው ሁኔታ ሰፍቶ ይንሰራፋል:: በነካሌብ ዘመን የነበረው ብቻ ሳይሆን ከዚያም በላይ ይሆናል:: ወገኔ! ይግረምህ አምላክህ ይህንን ያደርጋል፤ ከዚህም አልፎ የሌሎች አገሮች ሁሉ እድልና እጣፈንታ በሙሉ የሚወሰነው እዚህ በታላቋ ኢትዮጵያ ይሆናል:: አለምም የኢትዮጵያ ምርኮና በረከት ይሆናል::

መዝሙር ዳዊት 36 (37) 9	ትንቢተ ሶፎኒያስ ምእራፍ 3
ኢሳኢያስ ምእራፍ 57	ኢሳኢያስ ምእ 62 ፡ ፩ - 5
መዝሙር ዳዊት 57 (58)	መዝሙር ዳዊት 56

ወገኔ ልብ ብለህ አስተውል ፈጣሪህ ለክብሩ ሊመሰገንበት በእውነት ወዶሃል ቅን ፍርዱንም እንደጸሃይ ሊያወጣ ወስኗል:: ስለዚህም እኔ ወንድምህ የምመክርህን ታናሽ ምክር አድምጥ!!

ለሰው ልጅ ሁሉ ፍቅር ይኑርህ ክፋትን፣ ጭካኔን፣ ስስትን፣ ምንዝርናን፣ ሌብነትን፣ መልካም ያልሆነውን ሁሉ ፈጽሞ ከራስህ አርቅ በእምነት ወንድምህ እህትህ ለሆኑ ለአገርህም መታመን ይኑርህ ከዚህ ሁሉ በላይ ፈጣሪ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ሃሳብህ በፍጹም ነፍስህ ውደደው!!!

ስለአሁኑ መሪዎቻችንና ስለ እጣፈንታቸው::

ስልጣንስ ወደእግዚአብሄር ልጆችና አገልጋዮች እንዴት ይዞራል!

የሚለውን ከዚህ በታች በዝርዝር ስለምናይ በአንክሮ ተመለከተው::

መላው አለም በሚስጥርም ሆነ በግልጽ ሲደክም ይህችን የተቀደሰች የተባረከች ምድር ኢትዮጵያን ለማጥፋትና ከምድረ ገጽ ፈጽሞ ለመፋቅ ነበር:: በነበር ቀረ እንጂ! አዝማቹም የቀደመው እባብ ዲያብሎስ ሆን ሁሌም ዘመቻው የሚያነጣጥረው በእግዚአብሄር ፈቃድና ሃሳብ ላይ እንዲሁም በሰው ዘር ላይ በሙሉ ነው:: ማንኛውም አገር ሰለጠነም አወቀም ከእኩያው ጋር ከሚጋጭ ይልቅ ይህችን ድሃ አገር ማጥፋት ቀዳሚ እቅዱ ያደርጋል:: ይህንንም ሲፈጽም ኖሮአል አሁንም ይህንኑ ተግባር ያለማቅዋረጥ ሲያደርግ ይታያል::

አረቡና የአረቡ አለም፣ አሜሪካና ወዳጆችዋ፣ ኤሽያዊውም፣ ጥቁሩ አፍሪካዊም ለኢትዮጵያ ያላቸው ሰሜት ሁሌም የደፈረሰ ነው ለምን ቢባል ኢትዮጵያ ሃገራችን በሁለመናዋ የተለየች ናትና!! እስቲ ፈረንጁን ከፈረንጁ አስተያዩት በባህሉ በስብእናው በሁለመናው ተቀራራቢ ነው:: አረቡንም እዩት ያው ነው ጥቁሩም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የሚታይበት፣ በኤሺያዊውም ተመሳሳይ ከስተት ነው የሚስተዋለው:: ከዚህ ሁሉ የምትለየው ኢትዮጵያና ህዝቦችዋ ብቻ ናቸው:: በእምነትም በባህልም በተፈጥሮ ንቃትም በታሪክም በሁሉም ትለያለች ስለዚህም ሁሉም የአለም ፖለቲከኞችና መሪ በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ጉዳይ ሲመጣ የጋራ ግንዛቤው በጋራ መጥላትን ነው:: ከዚሁ የህሊና ጥመት በሚመነጭ የጥፋትና የክፋት ስራ መስራት ነው::

ለምን ይህ ሆነ! ይህ የሆነው ሰዎችን በመንፈሳዊ ህሊናቸው እንዳይገዙ የቀደመው እባብ ስራውና ተግባሩ ነውና ከሞላ ጎደል ሁሉንም የአለም ክፍል በትከሻው መልክ ነድቶ ጠፍጥፎና ቀርጾ እንደሚሻው አድርጎታል እሱ ያቀደውንና ያስጨበጠውን እንደ ህልውናና እንደ እውነት ተቀብሎታል:: ስለሆነም ለሌላው አለም አባታቸው ዲያቢሎስ ስልሆነ የሱ ጠላት ደግሞ ጠላታችን ነው:: የጨለማው ገዢ የጨለማ ስራ መሪ ነው:: ስለሆነም የዚህን ተጻራሪ የሆነውን በኢትዮጵያ የሚታየውን፣ ብርሃናዊ እምነት አይቀበልም::

ኢትዮጵያ የብርሃን ሃገር ናት:: ዘመንን ሁሉ ቆርጦ የመጣውን እውነት የጨበጠች ፈጣሪ አምላካችን በየዘመኑ ያስጨበጣትን የብርሃን ህግና ቃል አጽንቶ የኖረች ናት:: በመሆኑም አለም ሁሉ ይህንን የእውነት መንገድ ስቶ በጨለማው የአለማዊ መንገድ በመሄዱና እውነትን በመናቁ ለኢትዮጵያ የተሰጠውን ጸጋ ስለአጣ ስራው ይህንን እድልና እውነት የጨበጠችውን ኢትዮጵያን አጥብቆ ይጠላል:: በዚህ መንፈስና ስሜት በመገዛት የተለያየ አይነት ጥቃት ይሰነዝራል:: በፈጣሪ ፊት የከበረውን እምነት (ተዋህዶ ኦርቶዶክስን) ያጸናች፣ በኑሮ ስርአትዋ በወንድማማችነት ፍቅር የተሞላች ዘወትርም ለፈጣሪያዋ ከልቡዋና ባለማቋረጥ እንደ መልካም ጠል በሚመነጭ የምስጋና ጸሎት እንደ ጅረት የምታፈስ የቅኖችና የየዋሆ አገር ነች:: በዚህም ዲያቢሎስ እጅግ ስለተጠላች የሰይጣን ልጅ ሁሉ ከአያት ቅድመ አያቶቹ ጀምሮ 7000 ሺውን ዘመን በሙሉ በፊታውራሪው ዲያብሎስ አማካኝነትና አዝማችነት ያለማቋረጥ ሲዘምትባት ኖሮዋል:: አሁንም የሚታየው እውነት የሄው ነው::

በዚህ አስከፊ የመከራና የችግር ወቅት በመፈተን ላይ ያለችው አገራችን ኢትዮጵያ ታላቁን የፈጣሪዋን ተስፋ ጨብጣ ያለች መሆኑን ሁሉ ያውቃል:: ታዲያ የዚች ታላቅ አገር የጥፋትዋ መሪዎች እነማን ናቸው?

የዛሬው መሪዎቻችን ፈጣሪን የማያውቁ፣ በጭካኔ የተሞሉ፣ ይህችን አገር የረገጡ፣ የጠሉ ባህልዋን እምነትዋን፣ ህልውናዋን የናቁ ናቸው:: በሃይላቸው ታምነው የሚገዙ ናቸው:: ለጥፋትም የተላኩ ናቸው::ህዝብ ለአምላክ አልታዘዝ ሲል ሲያምጽ ለመቅጣት ሲል ፈጣሪ ጨካኝ ገዢዎችን እንዲልክ ሁሉ፣ የኛዎቹም በዚሁ መስፈርት የመጡ ናቸው እንጂ በራሳቸው ጉልበት የቆሙ አይደሉም:: ለነሱ ግን ይመስላቸዋል:: ያውቁታልም ተልዕኮውን ግን አይረዱም:: የሚነዳቸውም የሚያዛቸውም ለዚሁ ተግባር የተመደበው አጥፊ መላእክ ነው::

ስለመሪዎቻችን፤ ስለባህሪያቸው ማንሳት ምንም አይጠቅምም:: ሁሉም ወገኔ ያውቃቸዋልና፣ ውሸትን በራሱ በክፉ ስራ የጸኑ መሆናቸውን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያውቃል:: እጣ ፈንታቸውን ማንሳት ሰአቱ ሰለሆነ የግድም ተገቢ ነው:: እነሱም ካልተረዱት ቢያውቁት መልካም ነውና!!

ልብ ብላችህ አድምጡ! ጊዜው ፍጹም የጨለመባችሁ መሪዎቻችን!! በቅድሚያ የምለው ቢኖር ስለእድል ፈንታችሁ ነው:: ሰው እንደመሆናችሁ መጠን እጅግ አዝናለሁ:: በዚህ የታሪክ አጋጣሚ ባትከሰቱ በተሻለ ጥሩ በሆነላችሁ ነበር!!

ይህ ያለንበት የታሪክ ወቅት በኢትዮጵያም ሆነ በመላው አለም እጅግ ትልቅና ቀድሞም ያልታሰበና ያልታየ ከብር የሚከሰትበትና የሚታይበት ወቅት ነው:: የጨለማው 7000(ሰባት ሺ) ዘመናት ተሸኝተው ለምህረትና በረከት የተሰጠው የሰው ዘር ለእረፍት ለ1000 (አንድ ሺ) ዘመን የሚዘልቅበት የመሸጋገሪያ ድልድይ ላይ እንገኛለን:: የሚሻገሩት ደግሞ እጅግ የበዙ ናቸው::

የዘመናችን የአገራችን አለቃና ምንዝሮች ግን ከሚሻገሩት ሳይሆኑ ከማይሻገሩት ናቸው:: እንዲያውም የሚገርመው በዚህ የመጨረሻ ሰአት እንኩዋን እራሳቸውን ለማሹለክ የሚያስችላቸውን ስራ ሲሰሩ አይታዩም፣ አይጸጸቱም ዛሬም ከፈጣሪ ጋር ሊዋጉ ይከጅላቸዋል:: የሚገርመኝም ይኸው ነው:: የምታሳዝኑትም በዚህ ነው::

ሰው እንዴት አያስተውልም! ሰው እንዴት ከፈጣሪው ጋር ደፍሮ ሊታገል ይሞክራል? ሰው እንዴት ወደ ረግረግ እየሰጠመ ለመዳን አይጥርም? እምትገርሙ ናችሁ:: ሁሉ ከእጃችሁ ይወጣል! ይተናል:: አንድህም አታመልጥም ወዴት ነው የሚመለጠው? በአለም ሁሉ ያለ ወንጀለኛ፣ አመጸኛና ሓጢያተኛ የዲያብሎስ ፊትአውራሪ እዚህ ኢትዮጵያ መጥቶ (ተገዶ) በፍርድ አደባባይ ይቆማል!! ቅን ፍርድንም ይቀበላል::

ታዲያ እናንተ ወዴት ትሄዳላችሁ? ተይዞ ፍርዱን ወደሚቀበለው ወደሚጠረገውና ወደሚጠፋው አለም እጅግ ያሳዝናል ያልኩትም ለዚህ ነው::

ብዙዎች አለቆች ወገናቸውን በድለውና አጥፍተው ወደሌላው አለም መሸሽ የተለመደና ሁሉም መሪ የሚያውቀው ዘዴ ነው:: ይህ ዘዴ ግን መሸበትና ወደ ታሪክ መዝገብ ተጣለ:: መሸሻ የለም ቢሸሽም የትም ስፍራ ቢሆን ከተደበቀበት ተይዞ ተዋርዶ ለፍርድ መቅረብ አይቀርም:: ይህን ደግሞ ለመትረፍ ያድላችሁ እንጂ ታዩታላችሁ:: መፍትሄውና የሚሻለው ግን ከዚሁ ከብርሃን ችሎት ቀርቦ ቅን የእግዚአብሄርን ፍርድ መቀበል ብቻ ነው:: ፈራጁም መሃሪውም እንደልባችሁ ምንነት የቅጣት መጠኑን የሚወስነው የሰራዊት ሁሉ ጌታ እግዚአብሄር ነው::

ጆት ታንክ ጠብመንጃ የታመነ ወታደር ሁሉም አብዋራ ናቸው:: አንዳቸውም አያድንዋችሁም:: መሪዎቻችን ከዚህ ሁኔታ የሚያወጣቸው ምንም ዘዴ የለም:: የዘራችሁት የአመጽና የክፋት ዘር በህዝበ እግዚአብሄር ላይ ያደረሰው ጥፋት ብዙ ደም፣ ብዙ እንባ፣ ብዙ የሰው ህይወት እንዲያልፍበት ሆኖአል:: ይህ ደግሞ በፈጣሪ ተመዝኗል፣ ፍርዱም ወጥቷል:: ስለዚህ ወደየትም ማምለጥ አይቻልም:: ዛሬ የታመናችሁበት ስልጣን እሳት ሆኖ ይበላችኋል:: ለሱ ብላችሁ የደከማችሁት ድካም ሁሉ መና ይሆናል:: የትም አኑሩት የትም ያከማቻችሁትን፣ የገነባችሁትን ለምህረት የታደለው ይበላዋል:: ያከማቻችሁበት አገርና ወገን ይጠፋል:: የሚረዳችሁ ሁሉ እንደ ጪስ ይተናል::

አድምጡኝ፤ ጆሮአችሁንም ከፈቱ፤ አይናችሁንም ግልጡ! ይህ ስልጣን በከንቱ ደከማችሁበት ነገ የሚሆነውን የማይቀረውን ልንገራችሁ::

በርግጥ ነው የምላችሁ፤ ይህንን ስልጣን አለምንም ሁኔታ ለማሰረከብ ለምናችሁ፣ ተንበርከካችሁ፣ ጮህችሁ ለመላቀቅ ትጥራላችሁ:: ነገር ግን በእናንተ ሃሳብና ምኞት አይሆንም:: ስልጣን ሰጪ፣ ስልጣን ነሺ ጌታ ስለሆነ በሚገባ ከተጎዳችሁበት በህዋላ ፈጣሪአችን ሲያዝን ብቻ እንረከባችኋለን እንጂ እኛ የልዑል ባርያዎች ስልጣን ስጡን ብለን አንለምንምም አናደርገውምም! ደግሞስ ከማን ነው የምንለምነው! ስልጣኑ የአባታችን የፈጣሪአችን እኮ ነው!! ይህንን ሁላችሁም ልታወቁት ይገባል:: በመሆኑም ስልጣኑ ከእናነተ ተነጠቆ ለልጆቹ ይተላለፍ ዘንድ በሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ችሎት ተወሰነ፣ ጸደቀ፣ ታተመ:: ቀሪው የሽግግር ጊዜ ነው:: ያ ደግሞ ዋጋ የምትከፍሉበት ወቅት ነው::

ይህ እንዴት ይሆናል! ሲሆን ታዩታላችሁ በደጃችሁ አይደለም እንዴ ሁሉም ነገር! ምን ጊዜ አለና መጠበቅ ብቻ ነው::

የእምነት ሰው በእምነት ዐይኑ ያያል! ከሃዲና ፈጣሪውን የማያውቅ የሚያይበት ዐይን ስለሌለው ድንገት ጨለማ እስከሚውጠው ድረስ እያፌዘና እያላገጠ፣ አሊያም በድንጋጤ ተውጦ ፍጻሜውን ይጠብቃል!

ይህ የፍርድ ቃል መሰራጨትና በህዝብ መታወቅ ከጀመረ ጀምሮ ጊዜው ስለተፈጸመ ወደ ተግባር መለወጥና ጠረጋው ይጀመራል!!!

ወገኔ ሁሉ እራስህን አዘጋጅ መጪው ጥፋት በአንደበት እንደሚነገረው ቀሎ የሚያልፍ አይደለምና!! ፈጥነህ እራስህን በፈጣሪ እጅ ጣል! የመዳኛው መንገድ አንድ ብቻ ነው:: እሱን በታመነው ለወደዱት፣ በእሳት አጥሮ ለሚጠብቀው የሰራዊት ጌታ ጉያ ገበቶ መሸሸግ ብቻ ነው!! በብርቱ እምመክረውም እማስጠነቅቀውም ይህንን ብቻ ነው::

አንድ ማሳሰቢያ ለመሪዎቻችን ልገልጽ እወዳለሁ!!

መንግስት እንደ መንግስት እራሱን ቢያስገዛ መልካም ነው፡፡ በግሌ ሀላፊነትን የማውቅና የዚህንም ሸክም የምረዳ ነኝ፡፡ ትዕግስትን ማድረግ ፈጣሪ አስተምሮኛል፡፡ ይሁንና ለረጅም ጊዜ ትግስትን የሚፈትን ስራ ስትሰሩ ቆይታችኋል፡፡ የደህንነት ሰራዊት፣ ወሬና መረጃ ለቃሚ፣ታጣቂ በማሰማራት ስልታዊ የማጥቂያ ዘዴ ቀይሳችሁ በኔ ላይ ስትሰነዝሩ፣ ስትዘምቱ ቆይታችኋል፡፡

ትዕግስትም ያልቃል ስለዚህ ከድርጊታችሁ ታቀቡ እላለሁ!! ይህንን የምለው ሰው ምንም ቢሆን ሲጎዳ ማየት ስለሚከብደኝ ብቻ ነው፡፡ አትሳሳቱ፣ እኔ ስለእናነት የማላውቀው የተደበቀ ነገር አለ ብላችሁ እንዳትገምቱ፡፡ ጭለማ ብርሃንን አይመረምርም፤ ብርሃን ግን ጨለማን ይመረምራል፡፡ ተሰውራችሁ ማናቸውንም ነገር ስታቅዱ፣ ስትወጥኑ፣ ስትወጡም፣ ስትገቡም፣ ህለማችሁንም፣ ሁሉንም ፍንትው አደርጎ ያሳየኛል፡፡ ልብ ልትሉ ይገባል እኔ መታገሴ እንጂ ፈጣሪን ለመጠየቅና ዋጋችሁን ወዲያው እንዲሰጣችሁ ለማድረግ የጥቂት ሰኮነዶች ጥያቄ ብቻ ነው፡፡ እኔ ከመሰለኝ በጎም ሆነ ክፉ አምላኬን ከጠየኩት ምንም የምከለከለው ነገር እንደሌለና ለኔ ለባርያው ለልጁ ጆሮም ከፍት ዐይኑም በኔ ላይ መሆኑን ልታውቁት እወዳለሁ፡፡ ስለዚህ ትዕግስቴን አትፈታተኑ፡፡ ስለኔ የምገልጽላችሁ ይህን፣ ያንን አደርጋለሁ የሚላችሁ የአየርም በሉት የምድር፣ የውሃም በሉት ወይም ጳጳስም ደብተራ እነዚሁም ሼኪ ሁሉም ይድከሙላችሁ፡፡ የት ድረስ እንደሚሄዱ አውቃቸዋለሁ እነሱም ያውቁታል፡፡ ስለዚህ የዲያቢሎስ ሰራዊቶች ላለቀባችሁ ጊዜ አትድከሙ! ቀዩን መስመር አልፋችሁ ለመሄድ ተቃርባችኋል ድካማችሁን አስቡ ለኔ አይገደኝም! ዙረያዬን ከእንግዲህ ድጋሚ የሚያነጋግረን ሰአት የለምና!!

- ይህንን የጽሁፍ መልእክት ስታነብ የፈጣሪህን ድምጽ መስማትህን እወቅ!!!
- በስሜት አትገንፍል፣ ራስህን ግዛ፣ ደስታህም በአግባቡ ራስህን በመግዛት ይሁን!!
- ትህትናን ልበስ፣ ለወንድምህ እዘን፣ በሚደርስበት ጉዳት አትደሰት ቢድን ኖሮ ወንድምህ ነበርና!!!
- የእግዚአብሄር ሰው በነገር ሁሉ እራሱን ያስገዛለና! አንተም ትዕግስተኛ ርሁርሁ ቸር ሁን!
- ለሌላው የሚጨነቅ እውነተኛ ነው፤ አንተም ወደ አመጽ አትሂድ፤ ስራውን ሊሰራ የወጣው **የእግዚአብሄር ሃይል** የስጋ ድጋፍን አይፈልግምና ተጠንቀቅ!!

ስለዚህ መልእክት መሰራጨት

ጌታ አንድ ምሳሌ መስሎአል ለሶስት ሰዎች መክሊት ሰጠ፡፡ እንደየአቅማቸው ሰጣቸው እንዲነግዱ፣ እንዲያተረፉ ሶስቱም በየፊናቸው ተሰማሩ፣ ሁለቱ ነገዱ አተረፉ ትርፋቸውንም ይዘው መጡ፡፡ ተመሰገኑበት ተሸለሙበት፡፡ አንዱ ግን ሰርቶ ነግዶ ከማትረፍ ይልቅ ደበቀ፤ ጌታ ሲጠይቀውም ያንኑ ጌታ የሰጠውን አንዱን መክሊት አቀረበ ጌታ ረገመው ተኮነነ፣ እድል ፈንታው ጨለማ ሆነ፡፡

ይኽን ያልከዋችሁ በከንቱ አይደለም ይህንን የሰራዊት ጌታ መልእክት ባላችሁ አቅም ሁሉ ለመላው ህዝብ አድርሱ፣ በትኑ!! በዚህ ንስሃ የሚገባ አለ ይድናልም፤ እናንተም ነገዳችሁ፣ አተረፋችሁ፣ ሌላው ደግሞ ይህን መልእክት ይሰማል ንስሃ ሰለማይገባ አይድንም ይፈረድበታል፡፡ በዚህም አትርፋችኋል፡፡ ምክንያቱም ፍርድ ያገኘው ተመክሮ ተነግሮት እንዲመለስ ተመክሮ ስለሆነ በዚህም ለፈጣሪያችሁ ሰለታመናችሁና ሰለታዘዛችሁ አትራፊ ናችሁ፡፡

ነገር ግን ደብቃችሁ በቤታችሁ ቀብራችሁ ብታኖሩት! እንደ ሃኬተኛው ሰው፣ መክሊት ቀባሪ ትሆናላችሁና ተጠንቀቁ፡፡ እግዚአብሄር የሚወደውና የሚደሰተው የሰማችሁትን አምናችሁ፣ ከተሳሳታችሁበት ፈጥናችሁ ስትመለሱና ሌላው ወንድማችሁ እንደናንተው እንዲድን ስትጥሩ በቻ ነው፡፡

- ለሌሎች ሃገሮች መልእክቱ በአግባቡ ይደርስ ዘንድ በአማርኛም፣ በእንግሊዘኛም አንብባችሁ በውጪ ላሉት ወገኖቻችሁም ሆነ ለሁሉም የሰው ዘር እንዲደርስ አድርጉ፡፡ በዘመኑ ዘዴም ተጠቀሙበት፡፡
- በፖስታ፣ በኢሜይል፣ በፋክስ ላኩት ይድረሰው ፍርዱን ይወቅ፣ አውቆም ይዳን አሊያም ሞትን ይቀበላል፡፡
- ዛሬ ነው የማትረፊያው ሰአት፣ ነገማ በምህረት የታሰበው ሁሉ ከምድርም ከሰማይም የሚፈስለትን በረከት ስለሚያግኝ እምትጨምርልት ምንድነው!!

የፈተናው ሰአት አሁን ነው እንዲድን መርዳት አሁን ነው፡፡ እሳቱ በሙሉ ሃይሉና በታላቅ ቁጣ ከመፍሰሱ በፊት፡፡

ቤት ሲቃጠል ከውስጡ ሰውን ለማዳን እንደሚደክም ሁሉ እናንተም ጣሩ፡፡ ላረጋግጥላችሁ የምወደው ምንም ጊዜ አለመኖሩንና ፍጹም መምዋጠጡን ነው፡፡

እኔና ወንድሞቼን ለማወቅ አትባዝኑ! አጠገባችሁ ስላለን በስራው ላይ ብቻ አትኩሩ!!

ወደው ሳይሆን ተገደው እንከዋን ለኢትዮጵያ ለባለጉዳዩ ህዝብ፣ ለመላዉ አለም ህዝብ ባላቸው መገናኛ ዘዴ ሁሉ በቀን አስር ጊዜ ያወሩታል፡፡ የአለም ህዝብ ሁሉ መሪም ተባለ ምንም ይሁን ነፍሱን ለመታደግ በጭንቀት የሚበረው ወደኢትዮጵያ ይሆናል!!

እድለኛ የኢትዮጵያ ህዝብ በእውነት የ ምትወደድ ህዘብ ነህ!!

እግዚአብሄር በስራችሁ ሁሉ ይባርካችሁ!! እመቤቴ ድንግል ማርያም ዘወትር በእቅፍዋ ታኑራችሁ!

ከከቡር ቃሉ የተጠቀሱትን (ከመጽሃፍ ቅዱስ) ጥቅሶች አስተውላችሁ አንብቡ!!

አስጀምሮ ላስጨረሰኝ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ክብር ምስጋና ይኹን

ዘወትር ከኔ ላልተለየችኝ እናቴ ድንግል ምስጋና ይሁን

ከታመነው የሰራዊት ጌታ እግዚአብሄር ባሪያና አገላጋይ

ተፈጸመ!!

የገጹ ብዛት 19 (አስራ ዘጠኝ) መሆኑን አትዘንጋ!!

ስታሰራጭ በፍጹም ከገጽ ኢታጉድል!!

በፊደል ግደፊት ላይ ሳይሆን በመልእክቱ ላይ ብቻ አተኩር!!